# የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (የሥልጠና ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ
# (የሥልጠና ሞጁል)

**ህዳር 2017 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

# በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

አዘጋጆች

ዶ/ር ይልቃል ሙሉዓለም (ጎንደር ዩኒቨርስቲ)

ዶ/ር ጀሚላ ሁሴን (ሲቪል ሰርቪሲ ዩኒቨርስቲ))

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኋላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ

© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

ህዳር 2017 ዓ.ም

**ማዉጫ**

**የሞጁሉ አጠቃላይ መግለጫ ....... i**

**ምዕራፍ አንድ፡ የሙስና ወንጀል ምንነት ....... 1**

1.1. መግቢያ ....... 1

1.2. የሙስና ወንጀል ምንነት ....... 2

1.3. የሙስና ዓይነቶች ....... 3

1.4. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት ....... 7

1.5. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ....... 9

**ምዕራፍ ሁለት፡ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሙስና ስጋቶች ....... 18**

2.1. መግቢያ ....... 18

2.2. በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሙስና ስጋት ....... 19

2.3. በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሊከሰት የሚችል የሙስና መገለጫዎች ....... 23

2.3. ማጠቃለያ ....... 25

2.4. የማጠቃለያ ጥያቄዎች ....... 25

**ምዕራፍ ሶስት ፡ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚከሰቱ ሙስናዎች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅዕኖ እና የሙስና መከላከያ ስልቶች ....... 27**

3.1. መግቢያ ....... 27

3.2 በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚከሰቱ ሙስናዎች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅእኖ 28

3.3 በአስረጅ ናሙና (ኬዝ) ላይ የተመሰረተ ልምምድ ....... 35

3.4 የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከያ ስልቶች ....... 40

3.5. ሙስናን በመከላከል የሰራተኞች ሚና ....... 46

3.6. ማጠቃለያ ....... 50

3.7. የማጠቃለያ ጥያቄዎች ....... 51

**ማጣቀሻዎች ....... 53**

# የሞጁሉ አጠቃላይ መግለጫ

## I. መግቢያ

ሙስና የመንግሥትና የህዝብ ሃብትን የግል ወይም የቡድን ፍላጎትን በህገወጥ መንገድ ለማሟላት መልካም ሥነ-ምግባር በሌላቸው ሰዎች በየትም አገር፣ በማንኛውም አይነት ተቋም እና በማንኛውም ጊዜ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ይህ ተቀባይነት የሌለው ተግባር ዓለም ከፍተኛ ወደሆነ የኢኖቬሽን፣ ዲጂታላይዜሽን እና ቴክኖሎጂ ሁኔታ ውስጥ እያመራ ባለበት ወቅት የሙስና አይነቱ፣ መገለጫዎቹ፣ የሚከናወንበት መንገድ እየረቀቀ መጧል፡፡ ስለሆነም የመከላከያ ስልቶቹም በዛው ልክ መዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሙስናን ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፡፡ ቴክኖሎጂ እና ዘመናዊ አሰራሮች በመንግስት እና በዜጎች መካከል፣ በመንግስት ተቋማት እና በማህበረሰብ ተዋናዮች መካከል ያለውን የመረጃ ፍሰት ያመቻቻል፡፡ በዚህም የተነሳ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና የዜጎችን ተሳትፎ ያጎለብታል፡፡ በተጨማሪም ቴክኖሎጂ መረጃን ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ፣ የመንግስት አሰራሮችን ዲጂታል በማድረግ፣ የተንዛዛ አሰራርን በማስወገድ እና ብልሹ አሰራሮችን ሪፖርት ማድረግን በማስተዋወቅ የሙስና መከላከል ትግሉን ለማጠንከር አስችሏል፡፡ በተቃራኒው ዘመናዊ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የተከሰቱ ጥፋቶችን ለመደበቅ፣ ብልሹ ወይም የተጭበረበሩ ግብይቶችን ለማድረግ እና የመንግስት ዲጂታል አገልግሎቶችን ሆን ብሎ ለመጥለፍና ለመመዝበር እድል ስለሚፈጥሩ የሙስና መስፋፊያ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የፈጠራ እና የቴክሎጂ ምርምር የመጨረሻ ውጤቱ በእርግጠኝነት ስለማይታወቅ ሂደቱ ለሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡

የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የኢኖቬሽን እና ቴኬኖሎጂ ሚኒስቴር እና በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማትን ማለትም የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት፣ባዮ እና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣንን የሚያካትት ሲሆን ዘርፉ በአጠቃላይ የሀገሪቱ የዲጂታል ኢኮኖሚ የሚገነባበትን ከባቢያዊ ስርዓት መፍጠር፣ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ልማት ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የሚያስችል አቅም መገንባት እና ኢኖቬሽን፣ ቴክኖሎጂ እና ምርምር ለስራና ሀብት ፈጠራ አበርክቶ እንዲኖራቸው ማድረግ ተልዕኮዎች አሉት፡፡ የሚኒስትር መስሪያ ቤቱም ይሁን የተጠሪ ተቋማቱ ሰራተኞች ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ዘርፉ ላይ ከሚሰጡ ልዩ አገልግሎቶች

አንፃር ዘርፉን  የሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ይህ የስልጠና ሞጁል በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ለሚሰሩ አመራርና ሰራተኞች ስለ ሙስና ምንነት፣ የዘርፉን የሙስና ተጋላጭነት፣ ቴክኖሎጂ ሙስናን ለመከላከል ያለው ሚና እና የሙስና መከላከያ ስልቶች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር በየተቋሞቻቸው ሙስናን መከላከል እንዲችሉ ለማድረግ የተዘጋጀ የስልጠና ሰነድ ነው፡፡

## II. የሞጁሉ አላማ

ሰልጣኞች በዚህ ሞጁል ውስጥ የተካተቱ ትምህርቶችን ካጠናቀቁ በኂላ ስለሙስና ምንነት፣ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ለሙስና የሚያጋልጡ ምክንያቶች እና መከላከያ ስልቶችን እውቀት እና ክህሎት በመያዝና የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ራሳቸውን ከሙስና እንዲጠብቁ እንዲሁም በዘርፉ የሚደረጉ የሙስና መከላከል ስራዎችን እንዲደግፉ ማስቻል ነው፡፡

## III. ንዑስ አላማ

ስልጠናውን ከተከታተሉ በኂላ  ተሳታፊዎች

- ✓ የሙስና ዓይነቶችን፣ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚከሰቱ የሙስና አይነቶች መገለጫዎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የሙስና መንስኤዎችንና የሚያደርሰውን አሉታዊ ተጽዕኖዎች ይዘረዝራሉ፡፡
- ✓ በዘርፋቸው ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ ስልቶችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የእለት ተዕለት ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሙስናን በመከላከል ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና ይገነዘባሉ፡፡

## IV. ስልጠናው የሚሰጥበት ዘዴ

ስልጠናው 12 ሠዓት የሚፈጅ እና ሰልጣኝ ተኮር በሆነ መንገድ የሚሰጥ ሲሆን ሞጁሉ ሰልጣኞች እንዲማሩ የሚያስችሉ በየርዕሶቹ በዘርፉ ውስጥ በተግባር ከተፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች፣ ከታዩ ብልሹ አሰራሮች ወይም ከሌሎች አገሮች ተሞክሮዎች ለማስተማሪያነት በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተው የቀረቡ የመወያያ ጥያቄዎች፣ የተለያዩ ተግባራት፣ መልመጃዎችና አስረጅ ናሙናዎች (ኬዞች) ተካተውበታል፡፡
ስለሆነም ስልጠናውን ለመስጠት የአዕምሮ ጓዳ ማንኳኳት (Brainstorming)፣ ገለጻ፣ እና ውይይት የሚጠቀም ሲሆን የአሰልጣኞች ሚና የዕውቀት ባለቤትነት ሳይሆን ስልጠናውን የማሳለጥ ድርሻ ብቻ ይሆናል፡፡ ስልጠናው ሲጠናቀቅ ሰልጣኞች ራሳቸውን የሚገመግሙበት ቼክ-ሊስት እንዲሁም ሰልጣኞች በጋራ የሚወያዩባቸው ጥያቄዎች ተያይዘዋል፡፡

## V. ተተኳሪዎች

የዚህ ሞጁል ተተኳሪዎች በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሥር የሚገኙ ተቋማት አመራርና ሰራተኞች ናቸዉ፡፡

## VI. ለስልጠናዉ አስፈላጊ የሆኑ የማሰልጠኛ ቁሳቁሶች

ፍሊፕ ቻርት፣ ማርከር፣ ላፕቶፕ ኮምፒዉተር፣ ኤል ሲዲ ፕሮጀክተር፣ የተዘጋጀ ፓወር ፖይንት፣ ማስታወሻ ደብተር እና ብዕር ለስልጠናው አስፈላጊ ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# የሙስና ወንጀል ምንነት

## 1.1. መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀብል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምዕራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርቡበት ምዕራፍ ነው፡፡

**የምዕራፉ ዓላማ**

ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

1. የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፣
2. በአገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣

**የተፈቀደው ሰዓት**

ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 4:00 ሰዓት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

☞ **የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጠገባችሁ ካለ ሠልጣኝ ጋር ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡**

1. ጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
2. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ፡፡

## 1.2. የሙስና ወንጀል ምንነት

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግዕዝ የተወሰደ ቃል ነው፡፡ ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመሥጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመሥጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣ በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣ በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ መጠቀምን፣ ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን  የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል፣ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ *“… የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል…”* በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች፣ በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል፡፡ የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎች መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና አገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች፣ በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

## 1.3. የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption)፣ ሲስተሚክ (state capture) እና ፓለቲካዊ ሙስና ተብሎ ይከፈላል፡፡ ሆኖም በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው፡፡

### 1.3.1. ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት

መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግዢ፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂው ዘርፍ የሚስተዋለው ጥቃቅን ሙስና በአብዛኛው በዝቅተኛ ደረጃ ባለስልጣናት ወይም ሰራተኞች የሚፈጸሙ አነስተኛ ብልሹ አሰራሮችን ያካትታል። ይህም ብዙውን ጊዜ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚገለፅ ሲሆን እና የቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ቅልጥፍና እና ታማኝነት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**ምሳሌዎች፡-**

- ***ፈቃድ ለማዉጣት ጉቦ መስጠት፡-*** አንድ ኩባንያ የሶፍትዌር ወይም የቴክኖሎጂ ፈቃዶችን ማፅደቅ ለማፋጠን ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መደበኛውን የግምገማ ሂደት በመጣስ ትንሽ ጉቦ ሊከፍል ይችላል፡፡

**አንድምታ** (Implications) ፡-

- ለውጤታማነት ማነስ እና ለንግድ ስራ ወጪ መጨመር፣ በመጨረሻም ፈጠራንና የቴክኖሎጂ እድገት ላይ እንቅፋት ይሆናል፡፡
- ከሥነ-ምግባር ውጭ የሆኑ ድርጊቶች የተለመዱበት ሁኔታን ይፈጥራል፤ ሰራተኞች የተበላሹ ድርጊቶችን ሪፖርት እንዳያደርጉ ወይም የስነ-ምግባር ደረጃዎችን እንዳያከብሩ ያደርጋል፡፡

### 1.3.2. ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና አፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሻሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 “ከባድ የሙስና ወንጀል” ማለት፡-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፣ ኢኮኖሚ፣ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል። በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚስተዋለው ክፍተኛ ሙስና በከፍተኛ ደረጃ ላይ ባሉ ባለሥልጣኖች ወይም ሥራ አስፈፃሚዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እና ውስብስብ ኮንትራቶችን የሚያካትቱ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የፋይናንስ ጥፋቶችን ያካትታል።

**ምሳሌዎች፡-**

- **ፕሮጀክት ለማሸነፍ የሚፈፀሙ ትላልቅ የጉቦ ተግባራት፡-** አንድ የቴክኖሎጂ ድርጅት ለመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ለማግኘት ለመንግስት ባለስልጣናት ብዙ ገንዘብ የሚከፈልበት የሙስና ድርጊት ሊሳተፍ ይችላል። ለምሳሌ ብሄራዊ ብሮድባንድ ኔትወርክ መገንባት።
- **የገንዘብ ምዝበራ፡-** ከፍተኛ ባለስልጣኖች ለቴክኖሎጂ ልማት ወይም ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ውጥኖች የተመደበውን ገንዘብ ለግል ጥቅም ወይም ወደ ባህር ማዶ አካውንቶች በማዘዋወር ሊወስዱ ይችላሉ።

**አንድምታ** (Implications) ፡-

- ከፍተኛ ሙስና ወሳኝ ሀብቶችን ከቴክኖሎጂ እድገትና ልማት ፕሮጀክቶች በማራቅ የፈጠራ ስራን ያፍናል። ይህም በተቋማት ዉስጥ ጊዜ ያለፈበት ስርዓት እና መሠረተ ልማት ያስከትላል።
- የአገርን መልካም ስም በእጅጉ ይጎዳል፤የውጭ ኢንቨስትመንቶችን ያደናቅፋል፤ የኢኮኖሚ አለመረጋጋትን ያስከትላል።

### 1.3.3. ሥርዓታዊ ሙስና (systemic capture)

የአገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ሥርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው። ሲስተሚክ ሙስና ህግ

አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡ ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርዓታዊ (systemic capture) በመሆን መንግስትን ሲቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

### 1.3.4. ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂው ዘርፍ የሚስተዋለው የፖለቲካ ሙስና የመንግስት ባለስልጣናት ለግል ወይም ለፖለቲካዊ ጥቅማቸው ሲሉ ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን ወይም ሀብቶችን መጠቀሚያ ማድረግን ያካትታል፡፡ ይህም በቴክኖሎጂ ፈጠራ እና ልማት አቅጣጫ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡
**ምሳሌዎች፡-**

- **የቁጥጥር ሥርዓትን መቆጣጠር** (Regulatory Capture)፡- የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ባለሥልጣኖቻቸውን የንግድ ሞዴሎቻቸውን ሊነኩ የሚችሉ የመረጃ ጥበቃ ሕጎችን በሥራ ላይ ማዋልን የመሳሰሉ ጥቅሞቻቸውን የሚጠቅሙ ደንቦችን እንዲያዘጋጁ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡
- **በቴክኖሎጂ ድምጽ መግዛት፡-** ፖለቲከኞች ድምጽ ለመግዛት የቴክኖሎጂ መድረኮችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ነፃ የኢንተርኔት አገልግሎት መስጠት ወይም ለምርጫ ድጋፍ ምትክ መሳሪያዎችን መስጠት፣ በዚህም ዴሞክራሲያዊ ሂደቶችን ማዛባት፡፡

አንድምታ፡-

- የፖለቲካ ሙስና የተወሰኑ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን ከሌሎች ይልቅ የሚያበረታታ ፖሊሲ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፤ ይህም በዘርፉ ያለውን ውድድር እና ፈጠራን ይገድባል።
- ህዝቡ በመንግስትም ሆነ በዘርፉ ላይ ያለውን አመኔታ ያሳጣ ሲሆን ከቴክኖሎጂ ውጥኖች እና ፖሊሲዎች ጀርባ ስላለው ጥርጣሬ እንዲፈጠር ያደርጋል።

## 1.4. የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ የሆነ ወንጀል ነው። የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያደርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር፣ ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ። የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

### 1.4.1. የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ። በዚህ ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያስችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ። የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ። ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላለዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል።

### 1.4.2. የሙስና ወንጀል የሚያስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መጓደልን ያስከትላል። ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል። ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል። ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደርሳቸዉ ያደርጋል። በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል።

### 1.4.3. የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው፡፡ እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዝርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም የሚሰጣቸው ነው፡፡ ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### 1.4.4. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክንያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

“የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም” የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በህዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ በእጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### 1.4.5. ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመንዛዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ

ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

## 1.5. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመላክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

### 1.5.1. በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኂላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.5.2. ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.3. የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኂላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.4. አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ፣ የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ፣ ንብረት ጠባቂ፣ ወይም አጣሪ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት)፣ ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚያረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ጉዳይ ለማድረግ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.5. የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣ የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.6. አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን

ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 1.5.7. በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም

የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንቀሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.8. በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት፦

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤

በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣ የንግድ ስምምነት፣ የስራ ጨረታ፣ የዕቃ ማቅረብ ዉል፣ ወይም ሌላ ጥቅም ወይም

በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን፣ ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.9. በህገወጥ መንገድ መሰብሳብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤

ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረክብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.10. ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት፣ በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ፣ ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ያጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.11. ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.5.12. ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.13. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤
ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.14. የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት፣ ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ፣ ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኋላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.15. መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)

ማንኛዉም ሰው  የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፡፡

አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፣ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.16. መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ፣ ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.5.17. ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ፣ የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠይቅም፡፡

### 1.5.18. ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.5.19. ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ፣ ዋጋ ያለዉ ነገር፣ አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ ወይም ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ፣ ያገናኘ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.5.20. በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛውም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡

### 1.5.21. በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ይጠየቃል፡፡

ሰጭውም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፡፡

### 1.5.22. በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)

ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.5.23. ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡

### 1.5.24. ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡

### 1.5.25. በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ ስለመርዳት (አንቀጽ 33)

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

**ማጠቃለያ**

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆነም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. ያለአግባብ ጉዳይን ማንተት" በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉና የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀልን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሙስና ስጋቶች

## 2.1. መግቢያ

ሙስና ማለት በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል ሲሆን ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች በዚህ ኢ-ስነምግባራዊ ተግባር ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ማንኛውም ድርጅት ትልቅም ይሁን ትንሽ፣ መንግሥታዊም ይሁን የግል፣ ከተሰማራበት ዘርፍ ባህሪ ወይም ከውስጥ የአሠራር ሒደቱ ደካማ መሆን የተነሳ ለሙስና ሥጋት ተጋላጭ ነው፡፡ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ እና በስሩ የሚገኙ ተቋማት በሀገሪቱ ፈጠራ እና ቴክኖሎጂን የተመለከተ ጉዳዮች ላይ የፈቃድ እና የብቃት ሰርተፍኬት መስጠት፣ መቆጣጠር፣ ፈጠራ እና ቴክኖሎጂነክ ምርምሮችን ማከናወን እና የአገሪቱን የዲጂታላይዜሽን ሂደት ማስተባበር ኃላፊነት ያላቸው ሲሆን ይህንን ተግባራት በሚያከናውኑበት ጊዜ ተቋሞቹ እና ሰራተኞቻቸው ለሙስና ተጋላጭ የሚሆኑበት ሁኔታዎች አሉ፡፡

የሙስና አደጋን መገንዘብ ለተቋማት በተለይም እንደ ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ባሉ ዘርፎች ውስጥ ውስብስብ የሆኑ ፕሮጀክቶች፣ የቁጥጥር እና ፈቃድ ስራዎች ለብልሹ አሰራር ብዙ እድሎችን ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም ሙስናን በብቃት ለመከላከል ዘርፎች ወይም ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን ሁኔታ በውል መረዳት ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም በዚህ ክፍል ከኢኖቬሽን እና ከቴክኖሎጂ ዘርፍ ጋር የተያያዙ የሙስና ስጋት በዝርዝር ይዳስሳል፡፡

**የምዕራፉ አላማዎች**

ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች፡-

1. ለሙስና አስተዋጽዖ የሚያደርጉ መንስኤዎችን ይለያሉ፣
2. በዘርፉ የሚታዩ የሙስና ስጋቶችን ይተነትናሉ፣

**የተፈቀደው ሰዓት**

ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበለት ጊዜ 4፡00 ሰዓት ነው፡፡

### የማነቃቂያ ጥያቄዎች

☞ **የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጠገባችሁ ካለ ሠልጣኝ ጋር ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡**

1. ሰዎች የሙስና ተግባር ውስጥ ለምን ይገባሉ ብለው ያስባሉ?
2. የሙስና ስጋት ምንድን ነው?
3. በዘርፋችሁ/በተቋማችሁ ምን አይነት የሙስና ስጋት አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. በዘርፉ ምን ምን አይነት የሙስና ተግባራት ይስተዋላሉ?
5. የሙስና ስጋትን ቅድሚያ መለየት ምን ጠቀሜታ አለው?

## 2.2. በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሙስና ስጋት

የፌደራል ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽን በ2015 ዓ.ም በተለያዩ ዘርፎች ላይ ባደረገው የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት መሰረት የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ከታች በተመለከቱ ምክንያቶች የሙስና ስጋቶች ያሉበት መሆኑን ያሳያል፡፡

### ሀ. የተጠናከረ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አለመኖር

በየተቋማት የሚቋቋሙ የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋም ውስጥ ሙስና ስጋቶችን በመለየት የመከላከያ ስልቶችን የመንደፍ እና ሙስና በክሰቱ ሲታወቅም አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ አለባቸው፡፡ በዘርፉ የሚገኙ ተቋማት በኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ስር የሚገኙ አምስት ተቋማት ሁሉም የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ያቋቋሙ ቢሆንም በሰው ኃይል እና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች የተሟሉ አለመሆን እንዲሁም ሀላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል የበጀት ቁመና ላይ አለመሆን በዘርፉን የሥነ-ምግባር ጥሰቶችና እና የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮችን ለመከላከል አዳጋች ስለሚያደርገው ዘርፉን ለሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡

### ለ. ዝቅተኛ ተቋማዊ ተጠያቂነት መኖር

በዘርፉ ባሉ ተቋሞች ውስጥ ዝቅተኛ ተቋማዊ ተጠያቂነት መኖር የሙስና ስፋት ነው፡፡ ሰራተኞች በግልም ሆነ በቡድን ለደረገት የሙስና ተግባር ተጠያቂነነት አለመኖር ሌሎችም ሰራተኞ ወደ ሙስና እንዲገቡ በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

### ሐ. የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት የማድረግ ዝቅተኛ ልምድ

የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ ተቋማት የሙስና ተግባርን ቀድመው እንዲከላከሉ የሚያስችል ውጤታማ ስልት በጥናት ላይ ተመስርተው ለመንደፍ ያስችላል፡፡ ሆኖም በዘርፉ የሙስና ዳሰሳ ትናት የማከናወን እና በዛ ላይ ተመስርቶ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከያ ስልት የመንደፍ ልምድ ዝቅተኛ ስለሆነ ዘርፉን ለሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡

### መ. ወቅቱን የመሰለ የስነ-ምግባር ደንብ አለመኖር

በተቋም ውስጥ የሰራተኞች የስነ ምግባር ደንብ መኖር ሰራተኞች ከነሱ የሚጠበቁ እና የማይጠበቁ ተግባራትን እንዲያውቁ እና ደንቡን ባይከተሉ የሚደርስባቸውን አስተዳደራዊ እርምጃ የሚሳውቅ በመሆኑ በተቋም ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ሙስናን ለመከላከል ያግዛል፡ ይሁል እንጂ በዘርፉ የሚገኙ ተቋሞች የሥነ-ምግባር ደንብ ያዘጋጁ ቢሆንም ደንቦቹ ወቅታዊ አለመሆናቸው እና በሰራተኛው በኩል ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ ዘርፉን ለሙስና ስጋት ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡

### ሰ. ቅሬታዎችና ጥቆማዎች የሚቀርቡበት ስርዓት ውጤታማ አለመሆን

በዘርፉ ውስጥ ያሉ ተቋማት የቅሬታና ጥቆማ አቀራረብ ስርአት የዘረጉ ቢሆንም ለቀረቡ ጥቆማዎች እና ክሶች አጣርቶ እልባት የመስጠት ውስንነት መኖር ለመልካም አስተዳደርና ለሙስና በር ይከፍታል እንዲሁም የጠቋሚዎችን ጥቆማ የማቅረብ ፍላጎትና ተነሳሽነት ይቀንሳል፡፡

### ረ. የተቋማት ግልጽነት ዝቅተኛ መሆን

የዘርፍ ግልፅነት ለማሳደግ የዜጎች ቻርተር የተዘጋጀ ቢሆንም ተጠቃሚውጋ ተደራሽ ባለመደረጉ ዜጎች አገልግሎት በሚያገኙበት ጊዜ ግዴታቸውና መብታቸውን ስለማያውቁ ለአላስፈላጊ እንግልትና ብልሹ አሰራር እና ሙስና ተጋላጭ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል እና ሌሎች አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ለተቋማት ማህበረሰብና ለተገልጋዮች የግንዛቤ ስራ ስላልተሰራ እነዚህ አካላት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን እንዳይሳተፉ እና በመከላከል ሊኖራቸው የሚገባ ተሳትፎ እንዳይረዱ ስለሚያደርግ ዘርፉን ለሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡ ለምሳሌ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ውስጥ ለተከናወኑ ተግባራት ቅጥር፣ ግዢ፣ ክፍያ፣ ፕሮጀክት ኮንትራት የመሳሰሉት ማስረጃዎች እንዲያቀርብ ሲጠየቅ አለማቅረብ/ አለመኖር የብልሹ አሰራር መገለጫ ስለሆነ ለሙስና አጋላጭ ይሆናል፡፡

### ሠ. ደካማ የግዥ አስተዳደር እና ውስብስብ የግዢ ሂደት

በዘርፉ ውስጥ በአብዛኛው በተቋማት የሚፈፀሙ ግዥዎች በገበያ ጥናት ላይ ያልተመሰረቱ መሆናቸው, የፕሮጀክት ግዢዎችን ከመመሪያ ውጪ ያለምንም የጨረታ የፕሮፎርማ ውድድርየማከናወን ልምድ እንዲሁም ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልግጊ ግብአቶችን እንደየ ፕሮጀክቱ አይነት በዓመታዊ የግዢ እቅድ ውስጥ በማካተት በግዥ መመሪያው መሰረት ድዥ አለመፈፀሙየዘርፉን የግዢ ስርዓት ለሙሰና እና ብልሹ አሰራሮች ተገጋለጭ ሊያደርጋቸው ይችላል። ለምሳሌ በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ከአንድ አቅራቢ በተደጋጋሚ ግዥዎች የሚፈፀሙበት ሁኔታዎች መኖራቸው ከፍተኛ የመንግስት መዋዕለ ንዋይ የሚፈስበት የስራ ዘርፍ ህጋዊ አሰራርና ስርዓትንተከትሎ የማይሰራ ከሆነ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል።እንዲሁም ለጥቅም ግጭት ሊያጋልጥ ይችላል።

በተጨማሪም በቴክኖሎጂ ግዥ ውስጥ፣ ቴክኖሎጂ ላይ እየመጣ ያለው ለውጥ አሁን ያሉትን ደንቦች እና የቁጥጥር ስልቶችን በልጦ ስራ ላይ ያሉ ደንቦች እና የቁጥጥር ስርአቶች ላይ ክፍተት በመፍጠር ዘርፉን ተጋላጭ ያደርገዋል። የቴክኖሎጂ ኮንትራቶች ብዙውን ጊዜ ውስብስብ ውሎችን እና ሁኔታዎችን የሚያካትቱ ሲሆን ይህም ብልሹ አሰራርን በቀላሉ እንዳይታወቅ ያደርገዋል። እንዲሁም የብዙ የቴክኖሎጂ ፕሮጄክቶች ቴክኒካል ባህሪ ሂደቶችን ሊያደበዝዝ ስለሚችል ባለድርሻ አካላት እንቅስቃሴዎችን በብቃት ለመከታተል ፈታኝ ያደርገዋል።

### ሸ. የሰው ሀብት አስተዳደር መመሪያዎች የትግበራ ክፍተት

ተቋማት የመደበኛም ሆነ የፕሮጀክት ሰራተኞቻቸውን በሚቀጥሩበት ግዜ ተገቢውን መመሪያ በመከተል በቅጥር ሂደቶች ሊከሰቱ የሚችሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ን ለመቀነስ ይችላለሁ። ዘርፉ ውስጥ ከተደረገ የኦዲት ምርመራ ውጤት መሰረት የፕሮጀክት ኮንትራት ቅጥሮች በአብዛኛው በሪኮመንዴሽን የሚከናወን መሆኑ ሂደቱ ፕሮጀክቶች ብቁ የሆኑ ሰራተኞች እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ሂደቱ ለአድሏዊነት የተጋለጠ ሊሆን ስለሚችን ዘርፉን ለሙስና ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል።

### ቀ. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ልምድ ዝቅተኛ መሆን

ዘመናዊ ከሆኑ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከያ ስልቶች መካከል አንዱ የሚመለከታቸው አካላት የሀብት ማሳወቅና ማስመዝገብ ነው። ይሁን እንጂ በዘርፉ መመዝገብ ከነበረባቸው 1258

ሰራተኛናኃላፊዎች የተመዘገቡት 531 ብቻ (42%) መሆናቸው ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ለመቆጣጠር ስለሚያስቸግር ዘርፉን ለሙስና ስጋት ሊያጋልጥ ይችላል ።

**በ. ደካማ የፕሮጀክት አስተዳደር**

በዘርፉ ብዙ ፕሮጀክቶች እየተተገበሩ ቢሆንም በዘርፉ ባለው ደካማ የፕሮጀክት አስተዳደር ምክኒያት ፕሮጀክቶች ስለሚዘገዩ መንግስትን እና ህዝብን ለከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ እየዳረጉ ናቸው። በፌደራል ኦዲት ሪፖርት መሰረት ዘርፉ ውስጥ በተለይም በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ውስጥ

- የፕሮጀክት ክዋኔ መከታተያ መመሪያዎች አለመኖር ካላቸውም በአግባቡ አለመተግበር
- የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች መስፈርት ተዘጋጅቶ በመስፈርቱ መሰረት እንዲመረጡ አለማድረግ
- ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች በጀት መያዝ እና ወጪ መልቀቅ
- ፕሮጀክቶች ሳይጀመሩ ለረጅም ግዜ ወጪዎችን ማውጣት እና የአፈፃፀ ም ሪፖርት ማቅረብ
- ግዢዎችን እና ቅጥሮችን ያለውድድር ማከናወን
- ፕሮጀክቶችን የተመከለከት መረጃ አጠናክሮ አለመያዝ ለምሳሌ ፕሮጀክቶች ለምን እንደዘገዩ፣ መቼ እንደሚጠናቀቁ፣ ለቀሪው ስራ ምን ያህል ሀብት እንደሚያስልግ ወዘተ ተግባሮች እንደሚከናወኑ የተለየ ሲሆን እንዚህ እና ሌሎች ደካማ የፕሮጅት አስደዳደር ማሳያዎች ዘርፉን ለብልሹ አሰራር እና ሙስና ተጋላጭ ያደርገዋ።

**ተ. የውስጥ ኦዲትና ቁጥጥር ዝቅተኛ መሆን**

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና ሕጋዊና ጤናማ የሆነ የገንዘብና የንብረት አያያዝ እንደተከተሉ ለማረጋገጥ የፋይናንስና ንብረት ክንውን የውስጥ ኦዲት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም የስራቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ለዚሁ ተግባር በተቋቋመየውጭ ኦዲተር የማስገምገም ግዴታ አለባቸው። በዘርፉ ተቋማት ውስጥ የመደበኛ ተግባራት የውስጥ ኦዲት የሚከናወን ቢሆንም የፕሮጀክቶች ክዋኔ ኦዲት ስለማይደረግ በመሆኑ በፕሮጀክት አፈፃፀም ወቅት የሚከሰቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በወቅቱ ለመለየት እና የማስተካኬ እርምጃ ለመውሰድ አስቸጋሪ ስለሚደርገው ዘርፉን ለሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል።

## 2.3. በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሊከሰት የሚችል የሙስና መገለጫዎች

1. **ጉቦ**

- በግዢ ኮንትራት አሰጣጥ የሚፈፀም ጉቦ፡ በግዥ ሂደት የሳተላይት ቴክኖሎጂ እና አገልግሎቶች ኮንትራቶች የሚሰጡት ካለዉ ትክክለኛ ዉድድር ወይም ከሚያስገኘዉ ጥቅም ይልቅ ብልሹ አሰራርን መሰረት በማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡
- የቁጥጥር ተግባር በሚከናወንበት ወቅት/ ማፅደቂያዎች የሚፈጠር ጉቦ፡ በቁጥጥር ማፅደቆች ውስጥ ጉቦ የሚፈፀመው ባለሥልጣናቱ የቴክኖሎጂ የማፀደቅ ጥያቄዎችን ዉጤት ለማፋጠን ወይም ለመደገፍ ሕገ-ወጥ ክፍያዎችን ሲቀበሉ ነው፡፡
- ለምርምር ድጋፎች እና የገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥ የሚፈጠር ጉቦ : ለምርምር ድጋፎች ጉቦ የሚፈፀመው ግለሰቦች ወይም ፈንድ ፈላጊ አካላት ለምርምር የገንዘብ ድጋፍ አሰጣጥ ሂደት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ህጋዊ ያልሆነ ክፍያ ሲያቀርቡ ነው፡፡ ይህ አሰራር የፋይናንስ ሂደቱን ፍትሃዊነት የሚጎዳ እና ከጥቅም ይልቅ በፋይናንስ ማበረታቻዎች ላይ የተመሰረቱ ፕሮጀክቶችን መምረጥ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሙስና ፈጠራን ማደናቀፍ እና ውጤታማ ያልሆነ የሃብት ድልድል ሊያስከትል ይችላል፣ በመጨረሻም የምርምር ውጤቶችን ጥራት ይጎዳል.
- በፓተንት እና በንግድ ምልክት ምዝገባ ላይ የሚሰጥ ጉቦ፡ የባለቤትነት መብትና የንግድ ምልክት ምዝገባ ጉቦ የሚፈፀመው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን ለማፋጠን ወይም ለማፅደቅ ለባለስልጣኖች ህገወጥ ክፍያ ሲያቀርቡ ነው፡፡ ይህ የምዝገባ ሂደቱን ፍትሃዊነት እና ታማኝነት ይጎዳል፣ ይህም ህጋዊ ደረጃዎችን የማያሟሉ የፈጠራ ባለቤትነት ወይም የንግድ ምልክቶች እንዲፀድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ምሳሌ፡ በ2018 የአፍሪካ ህብረት ሪፖርት ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የንግድ ድርጅቶች የተፋጠነ የፈጠራ ባለቤትነት ፍቃድ ለማግኘት በጉቦ የሚሳተፉባቸውን ጉዳዮች አጉልቶ አሳይቷል፡፡ እነዚህ ተግባራት በአእምሯዊ ንብረት ሥርዓት ላይ እምነት ማጣትን ያስከትላሉ፡፡ [African Union Intellectual Property Reports, 2018]

2. **ማጭበርበር**

- የምርምር መረጃን ማጭበርበር፡ የምርምር መረጃዎችን ማጭበርበር የተፈለገውን ውጤት ለማግኘት ውጤትን ማጭበርበር ወይም መፍጠርን ያካትታል፡፡ ይህ የጥናቱን ትክክለኛነት ከመጉዳት በተጨማሪ በውሸት መረጃ ላይ ተመስርተው የተሳሳቱ የፖሊሲ ውሳኔዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡

- *ሪፖርቶችን ማጭበርበር፡*
  - *የፕሮጀክቶችን ያሉበትን ደረጃ እና ሁኔታ ለማሳሳት የፕሮጀክት መረጃዎችን እና ውጤቶችን በኦፊሴላዊ ሰነዶች ውስጥ ሆን ብሎ ማጭበርበር ያካትታል። ይህም ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍን ለማግኘት ወይም ተጠያቂነትን ለማስወገድ ሲሆን ይህ ድርጊት በመጨረሻም በሕዝብ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት የሚቀንስ ነው*
  - *የተገዢነት ሪፖርቶችን ማጭበርበር* (Falsification of Compliance Reports)፡ *የቁጥጥር ደረጃዎችን ማክበርን ለማመልከት ሆን ተብሎ የተዛባ መረጃን ያካትታል። ይህ የህዝብ ጤና እና ደህንነትን አደጋ ላይ ይጥላል፣ ምክንያቱም ባለድርሻ አካላት ስለ ምርቶች ወይም ሂደቶች ደህንነት እና ውጤታማነት ሊታለሉ ይችላሉ*
- *መዝገቦችን ማጭበርበር* (Falsification of Records)፡ *መዝገቦችን ማጭበርበር ከአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ ጋር የተያያዙ ኦፊሴላዊ ሰነዶችን መለወጥ ወይም ማዛባትን ያካትታል። ይህ በባለቤትነት ላይ አለመግባባቶችን ሊያስከትል እና የአእምሯዊ ንብረት ስርዓትን አስተማማኝነት ሊያሳጣው ይችላል። ምሳሌ፡ በ*2021 *በተደረገው ምርመራ የ*EIPA *ባለስልጣናት የንግድ ምልክት ምዝገባዎች ላይ የተወሰኑ አመልካቾችን ለማበረታታት መዝገቦችን በማስተካከል ላይ እንደሚሳተፉ አረጋግጧል።* [Source: Ethiopian Intellectual Property Authority Investigation Reports, 2021]
- *የምርምር ውጤቶች ማዛባት፡ የምርምር ውጤቶችን ማዛባት ጥሩ ውጤቶችን ለማምጣት መረጃን መቀየር፣መፍጠር ወይም መርጦ ሪፖርት ማድረግን ያካትታል። ይህ አሰራር የሳይንሳዊ ሂደቱን ታማኝነት የሚጎዳ እና በህዝብ ፖሊሲ እና ጤና ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል፣ ምክንያቱም በውሸት መረጃ ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎች ወደ ጎጂ ውጤቶች ሊመሩ ይችላሉ።*

3. **ምዝበራ**

- *የፕሮጀክት ገንዘብን ለግል ጥቅም ማዋል*
- *የተሳሳተ የበጀት ምደባ፡ ገንዘብ አላግባብ መመደብ የፋይናንሺያል ሀብቶችን አላግባብ መጠቀምን የሚያመለክት ሲሆን ይህም አብዛኛውን ጊዜ ከክትትል ማነስ ወይም ሆን ተብሎ ለግል ጥቅማጥቅም የሚደረግ ለውጥ ሲሆን ነዉ።*
- *የገንዘብ አያያዝ ጉድለት* (Mismanagement of Funds)፡ *የገንዘብ አያያዝን በአግባቡ አለመጠቀም በድርጅቱ ውስጥ የፋይናንስ ሀብቶችን በአግባቡ አለመያዙን ወይም መመደብን የሚያመለክት ሲሆን ይህም ወደ ውጤታማነት እና ተልእኮውን በብቃት መወጣት*

እንዳይችል ያደርጋል። ምሳሌ፡- በ2019 የኢትዮጵያ ዋና ኦዲተር የተደረገ ዲት ኢሕአፓን ጨምሮ በተለያዩ የመንግስት ኤጀንሲዎች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ አያያዝ ጉድለት አሳይቷል። ኦዲቱ በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ እና በአእምሯዊ ንብረት አስተዳደር ውስጥ ለአቅም ግንባታ የታቀዱ ሀብቶች አላግባብ መመደብ ልዩነቶችን በማሳየት የተሻሻለ የፋይናንስ ቁጥጥር አስፈላጊነትን አጉልቶ አሳይቷል። [ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ዋና ኦዲተር ሪፖርት፣ 2019]

4. **አድሏዊነት**

- በተደረጉ ዳሰሳዎች እና የፌደራል ኦዲት ሪፖርት መሰረት በዘርፉ በፕሮጀክቶች የሰራተኛ ቅጥሮችን እና መደበኛ እና የፕሮጀክት የእቃ እና የአገልግሎት ግዢዎችን ያለውድድር ማከናወን ይስተዋላል። ይህም ለአድሏዊነት ያጋልጣል።

## 2.3. ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል የሙስና ስጋት በተቋም የስራ ሂደቶች ውስጥ ታማኝነትን እና ተጠያቂነትን የሚጎዳ ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት ነው በማለት ገልፀነዋል። ተሳታፊዎች ስለ ሙስና ስጋቶች እና ለእንደዚህ አይነት ባህሪያቶች አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የተለያዩ የስጋት መንስኤዎችን ተምረዋል። የሙስና አደጋዎችን መለየት የታማኝነት ባህልን ለማዳበር እና በተቋማት ውስጥ ፈጠራን ለማስፋፋት አስፈላጊ በመሆኑ የሙስና ስጋት መከላከያ ስትራቴጂዎችን ለመተግበር ጠቃሚ ነው። ተቋማት የሙስና አደጋዎችን በመረዳትና በመፍታት ራሳቸውን ከህግ እና ከስም መጥፋት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የአፈፀም ውጤታማነታቸውን ማሳደግ ይችላሉ። ግልጽ የግዥ ሂደቶች፣ መደበኛ ኦዲት እና ስልጠናዎች ያሉ ስልቶችን መተግበር እነዚህን አደጋዎች በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚቀንሱ ተቋማት ለእድገት እና ለመተማመን ምቹ የሆነ የስነ-ምግባር ሁኔታን ለመፍጠር ያስችላቸዋል። በተመሳሳይ ሙስና የሚያከትላቸው አሉታዊ ጉዳችም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ተቋማዊ፣ የሰብአዊ መብት እና ቴክኖሎጂያዊ ተብለው በዝርዝር ተዳስሰዋል።

## 2.4. የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ይህን የስልጠና ክፍለ ጊዜ እንደጨረሱ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በመመለስ የክፍሉን የትምህርት አላማዎች ምን ያህል እንዳሳኩ እራስዎን የገልግሙ።

1. የሙስና ስጋት ምን ማለት ነው የሙስና ስጋት መንስኤዎች ምንድን ናቸው?

2. በተቋማችሁ ውስጥ በተለየ ሁኔታ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ለምን?
3. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍን ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉት ልዩ ምክኒያቶች አሉ ምንድን ናቸው?
4. በተቋም ውስጥ የሙስና ስጋቶችን በምን መንገድ እንለያለን? የሙስና ስጋቶችን የመለየት የማን ኃላፊነት ነው? መቼ ነው ልየታ የሚከናወነው?

# ምዕራፍ ሶስት

## በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚከሰቱ ሙስናዎች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅዕኖ እና የሙስና መከላከያ ስልቶች

### 3.1. መግቢያ

ሙስና ብዙ ዘርፎችን የሚዳስስ፣ መፈጸሚያ መንገዱም በየጊዜው እየተለዋወጠና እየረቀቀ የሚሄድ ወንጀል ነው፡፡ ለመከሰቱ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል፡፡

ችግሩ ከተከሰተ በኋላ የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

የሙስና አደጋን መገንዘብ ለተቋማት በተለይም እንደ ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ባሉ ዘርፎች ውስጥ ውስብስብ የሆኑ ፕሮጀክቶች፣ የቁጥጥር እና ፈቃድ ስራዎች ለብልሹ አሰራር ብዙ እድሎችን ይፈጥራል፡፡ በዚህ ክፍል ከኢኖቬሽን እና ከቴክኖሎጂ ዘርፍ ጋር የተያያዙ የሙስና ጉዳቶች፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች በዝርዝር ይዳስሳል፡፡

**የምዕራፉ አላማዎች**

**ከስልጠና በኋላ ሰልጣኞች**

1. የሙስና ጉዳቶችን ይዘረዝራሉ፣
2. የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
3. ሙስናን በመከላከል የዘርፉ ሰራተኞች የሚኖራቸውን ሚና ይገልፃሉ፣
4. የሙስና አደጋዎችን ለመቀነስ የሚያግዙ ስልቶችን ይተገብራሉ፤

**የተፈቀደው ሰዓት፡** ይህን ምዕራፍ ለማጠናቀቅ የተመደበው ጊዜ 8:00 ሰዓት

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

☞ **የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጠገባችሁ ካለ ሠልጣኝ ጋር ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡**

1. ሙስና ጉዳት አለው? የሙስናን ጉዳት በራስዎ ወይም በሚያውቁት ሰው ላይ ምን ያህል አስተውለዋል?
2. በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናዎች ማን ላይ ምን አይነት ጉዳት ያመጣሉ ብለው ያስባሉ?
3. ሙስናን መከላከል ይቻላል? እንዴት? የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡፡
4. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡
5. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡

## 3.2 በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚከሰቱ ሙስናዎች የሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅእኖ

የተለያዩ የጥናትና ምርምር ግኝቶች እንደሚያመለክቱት ሙስና ዘርፈ ብዙ የሆኑ ጉዳቶችን በማድረስ አብዛኛውን ህዝብ ለከፋ ድህነት ከመዳረግ አልፎ የሰውን ልጅ ህልውና የሚፈታተን አደጋ ነው፡፡ ሙስና የሚያደርሰው አሉታዊ ተፅዕኖ በዋናነት በአራት መልኩ ይታያል፡፡

### 1. ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ያለው ሙስና ኢኮኖሚያዊ መዘዞች ከፍተኛ ሲሆን፣ የድርጅቶችን የፋይናንስ ጤና የሚጎዳ፣ ኢንቨስትመንትን የሚገታ እና ለሰፋፊ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

### ሀ. ለድርጅቶች የገንዘብ ኪሳራ ያስከትላል

- **ቀጥተኛ ወጪዎች (ቅጣቶችና ህጋዊ ክፍያዎች)**:- ሙስና ብዙውን ጊዜ በድርጅቶች ላይ ከፍተኛ ቀጥተኛ የገንዘብ ቅጣት ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ 2016 ቮልስዋገን በአሜሪካ ባለስልጣናት በተለቀቀው የማጭበርበር ቅሌት ምክንያት በ 2.8 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቷል፡፡ አጠቃላይ ወጪዎች፣ የህግ ክፍያዎችን እና የማተካከያ ክያዎችን ጨምሮ፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ከ30 ቢሊዮን ዶላር በላይ አልፏል፣ ይህም ኩባንያው ለፈጠራ ስራዎች ኢንቨስት ከማድረግ ይልቅ እነዚህን ወጪዎች ለመሸፈን ብዙ ሀብቶችን እንዲመድብ አስገድዶታል፡፡
- **ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች (የሚያመልጡ እድሎች፣ የቢዝነስ ቅልጥፍና መቀነስ)**:- ሙስና ድርጅቶችን ከዋና ዋና ሥራቸው እንዲዘናጉ ያደርጋቸዋል፣ ይህም መልካም አጋጠሚዎች እንዲያመልጧቸው እና ውጤታማነታቸው እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ኖኪያ በየአገሩ ባሉ አጋሮቹ ብልሹ አሰራር ምክንያት በተለያዩ ገበያዎች የተወዳዳሪነት እና የፈጠራ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡፡ ምክኒያቱም በተለያዩ አገሮች ውስጥ የታየው የሙስና ክስተት ኖኪያ ጠቃሚ የሆኑ ኮንትራቶችን እና ሽርክናዎችን በማጣት አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር አቅሙ ላይ ተጽዕኖ አሳድሮበታል፡፡

### ለ. በኢንቨስትመንት እና በገንዘብ ድጋፍ ላይ ተጽዕኖ

- **የውጭ እና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንትን ይገታል**፡ ሙስና ኢንቨስተሮችን የማይስብ ያልተረጋጋ የንግድ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ለምሳሌ ዜድቲኢ ኮርፖሬሽን በጉቦ እና በማዕቀብ ጥሰት ውስጥ የተሳተፈ በመሆኑ እገዳዎች የገጠሙት ሲሆን ይህም የኢንቨስተሩን እምነት እንዲያጣ እና የአክሲዮኑ ዋጋ እንዲቀንስ አድርጓል፡፡
- **የካፒታል ዋጋ መጨመር**:- በድርጅት ውስጥ የሙስና ስጋት ካለ አበዳሪዎች ከፍተኛ ስጋት ስለሚኖራቸው ሙስና የካፒታል ወጪን ሊጨምር ይችላል፡፡ እንደ የዓለም ባንክ ከሆነ በሙስና የተዘፈቁ አካባቢዎች ውስጥ ያሉ ድርጅቶች በእነዚህ ስጋቶች ምክንያት እስከ 10% ተጨማሪ የብድር ወጪዎችን ሊከፍሉ እንደሚችሉ ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ፡ በሙስና በተሞላ ሀገር ውስጥ ጀማሪ የቴክኖሎጂ ድርጅት በተመጣጣኝ ዋጋ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ስለማይችል ይህም የማደግ እና የመፍጠር አቅሙን ይገድባል፡፡

### ሐ. የኢኮኖሚ አለመረጋጋት

- **በገበያ ውድድር ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ፡-** ሙስና ከሥነ ምግባር ውጭ የሆኑ ተግባራትን የሚፈጽሙ ኩባንያዎችን በመደገፍ የገበያ ውድድርን ያዛባል:: ለምሳሌ በህንድ ውስጥ ያለው የ2ጂ ስፔክትረም ማጭበርበር አንዳንድ የቴሌኮም ኦፕሬተሮችን የሚደግፉ ብልሹ አሰራሮችን ያካተተ ሲሆን ይህም ውድድርን እና ፈጠራን አዳክሟል::
- **በኢኮኖሚ እድገት ላይ የረዥም ጊዜ ተጽእኖ፡-** የረዥም ጊዜ ሙስና ሀብትን ከአስፈላጊ አገልግሎቶች በማራቅ የኢኮኖሚ እድገትን ሊያደናቅፍ ይችላል:: ለምሳሌ በናይጄሪያ በነዳጅ እና በጋዝ ሴክተር ውስጥ የተንሰራፋው ሙስና ሀገሪቱ ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት ቢኖራትም የኢኮኖሚ እድገቷን አግዷል:: የናይጄሪያ ብሄራዊ ፔትሮሊየም ኮርፖሬሽን በሙስና ምክንያት በቴክኖሎጂ እና በመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች ላይ ተፅዕኖ በማሳደሩ ውጤታማ ባለመሆኑ ይተቻል::

## 2. ማህበራዊ ጉዳቶች

### ሀ. የህዝብ አመኔታ መሸርሸር

- **በተቋማት ላይ ያለው የህዝብ አመኔታ ማጣት፡-** ሙስና ህዝቡ በመንግስታዊ ተቋማት ላይ ያለውን እምነት ያሳጣል:: ድርጅቶች ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ የግል ጥቅም እንደሚያስቀድሙ ዜጎች ሲገነዘቡ፣ የህዝብ አመኔታ ይቀንሳል:: ለምሳሌ የኢንሮን ቅሌትን በተመለከተ፣ የተንሰራፋው የድርጅት ማጭበርበር መንግስት በፋይናንሺያል ተቋማት እና ተቆጣጣሪ አካላት ላይ ከፍተኛ የሆነ ህዝባዊ እምነት እንዲያጣ አድርጓል፣ በቴክኖሎጂው ዘርፍም ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል:: የኢንሮን ቅሌት የፈጠረው ውድቀት በድርጅታዊ አስተዳደር ላይ ጥርጣሬ ጨምሯል እንዲሁም በባለሀብቶች መተማመን ላይ የተመሰረቱ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን ጎድቷል::
- **የዜጎች ተሳትፎ መቀነስ፡-** ዜጎች በተቋማት ላይ አመኔታ ሲያጡ እንደ ድምጽ መስጠት እና ማህበረሰብ ተሳትፎ ያሉ የሲቪክ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ እድላቸው አነስተኛ ይሆናል:: እንደ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የጥናት ግኝት ሰዎች በሙስና ስርዓት ውስጥ ድምፃቸው እንደማይሰማ ስለሚሰማቸው ሙስና ወደ ፖለቲካዊ ግድየለሽነት እንደያሚመራ አረጋግጧል:: ለምሳሌ፡ ከፍተኛ የሙስና መረጃ ጠቋሚ ባለባቸው እንደ

ብራዚል ባሉ አገሮች የዜጎች ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፣ ይህም ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን እና ተጠያቂነትን ጎድቷል።

## ለ. *ያልተመጣጠነ ተጽዕኖ እና ማህበራዊ ኢ-ፍትሃዊነት* (inequality and social injustice)

- ***በተገለሉ ቡድኖች ላይ የሚኖረው ያልተመጣጠነ ተጽእኖ፡-*** *የተገለሉ ማህበረሰቦች በሙስና የተዘፈቁ ስርዓቶችን ለመምራት የሚያስችል ሃብትና ሃይል ስለሌላቸው ሙስና ባልተመጣጠነ ሁኔታ ይጎዳቸዋል። ለምሳሌ፣ በብዙ ታዳጊ አገሮች እንደ ጤና አጠባበቅ እና ትምህርት ያሉ በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚፈጸሙ ሙስናዎች ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያለውን ልዩነት ያባብሳሉ። ለምሳሌ፡ በህንድ በሕዝብ ጤና አገልግሎቶች ውስጥ ያለው ሙስና ለድሃ ማህበረሰቦች በቂ የጤና አገልግሎት እንዳይሰጥ አድርጓል፣ ይህም ከበለጸጉ ህዝቦች ጋር ሲነጻጸር የከፋ የጤና ውጤቶችን አስከትሏል።*

- ***ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶችን ማስፋፋት፡-*** *ሙስና ሃብት ከህዝብ አገልግሎት ወደ ግል ጥቅም እንዲውል ስለሚያደርግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶችን ሊያሰፋ ይችላል። ሀብታም ግለሰቦች እና ኮርፖሬሽኖች ብዙውን ጊዜ በሙስና ተጠቃሚ የሚሆኑ ሲሆን የተገለሉ ቡድኖችንን ግን የበለጠ ወደ ኋላ ይተጎትታል፡፡ ለምሳሌ፡- በናይጄሪያ በነዳጅ ዘርፍ ያለው ሙስና የህዝቡን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ባለመቻሉ ትንሽ ልሂቃንን በማበልጸግ ከፍተኛ የሆነ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነት አስከትሏል።*

## ሐ. *የሰብአዊ መብት ላይ ያለው ተፅዕኖ*

- ***ኢ-ፍትሃዊነትን ያስቀጥላል፡-*** *ሙስና ወንጀለኞችን እንዳይቀጡ በማስደረግ የሰብአዊ መብት ረገጣን ሊያስቀጥል ይችላል። የመንግስት ባለስልጣናት ሙስና ሲፈጽሙ እራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን ከተጠያቂነት በመከላከል የፍትህ ስርአትን ያናጋሉ። ለምሳሌ፡ በሜክሲኮ፣ በህግ አስከባሪ አካላት ውስጥ ያለው ሙስና የአደንዛዥ ዕፅ አዘዋዋሪዎች ያለ ምንም ቅጣት እንዲሰሩ አስችሏቸዋል፣ ይህም ወደ ሰፊ ብጥብጥ እና የሰብአዊ መብት ጥሰት አስከትሏል።*
- ***በቴክኖሎጂ እና አገልግሎት ተደራሽነት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ፡-*** *ሙስና አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እና አገልግሎቶችን በተለይም ተጋላጭ ለሆኑ ህዝቦች ተደራሽነትን ሊገድብ ይችላል። ለቴክኖሎጂ ማሻሻያዎች ወይም ለዲጂታል መሠረተ ልማት የታቀዱ*

የሕዝብ ገንዘቦች ያለአግባብ ሊመዘብሩ እና ማህበረሰቡን አስፈላጊ አገልግሎቶች እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ለምሳሌ፡ በኬንያ፣ በዲጂታል አገልግሎቶች ግዥ ላይ ያለው ሙስና አስፈላጊ አገልግሎቶችን እንዳይዘረጉ እንቅፋት ሆኖበታል፣ ይህም የተገለሉ ቡድኖች የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ላይ ተጽእኖ አድርጓል።

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ያለው ሙስና የሚያስከትለው ማህበራዊ መዘዝ ከፍተኛ ሲሆን፣ ይህም የህዝብ አመኔታ እንዲታጣ፣ የእኩልነት መጓደል እና ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ችግር እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

### 3. ተቋማዊ ጉዳት

### ሀ. መልካም ስም ላይ የሚደርስ ጉዳት

- **በባለድርሻ አካላት ዘንድ ታማኝነት ማጣት፡-** ሙስና ባለሀብቶችን፣ደንበኞችን እና አጋሮችን ጨምሮ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ተአማኒነት በእጅጉ ይጎዳል። ለምሳሌ በሲመንስ AG የጉቦ ቅሌት ውስጥ ኩባንያው ኮንትራቶችን ለማስገኘት ሰፊ ጉቦ ሲፈጽም በመገኘቱ በባለድርሻ አካላት ዘንድ ያለው ከፍተኛ እምነት እንዲጠፋ አድርጓል።
- **የምርት ስም ጉዳት፡-** በሙስናው ዙሪያ የሚነገረው ያለው አሉታዊ መረጃ የድርጅቱን የረጅም ጊዜ የምርት ስም ላይ ጉዳትን ያስከትላል፣ የደንበኞችን ታማኝነት እና ገበያን ይጎዳል። ለምሳሌ፣ ከዌልስ ፋርጎ የውሸት መለያዎች ቅሌት በኋላ፣ ባንኩ ከፍተኛ የሆነ የደንበኞችን አመኔታ ማሽቆልቆል እና የብራንድ ስሙ እና ዝና እንዲበላሽ በማድረግ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ተፅኖን አስከትሎበታል። በተመሳሳይ በኢትዮ ቴሌኮም በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ግዥ ላይ የተፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች ላይ የመንግስት ባለስልጣናት በሙስና ተግባር መሳተፋቸው በኢትዮ ቴሌኮም ላይ ከፍተኛ ታማኝነት እንዲቀንስ እና ባለሃብቶች በመንግስት ይዞታ ስር ባሉ ድርጅቶች ላይ ያላቸውን እምነት እንዲጎዳ አድርጓል።

### ለ. የጠንካራ ሰራተኞች ሞራል መቀነስ እና ከስራ መልቀቅ

- **በስራ ቦታ ባህል ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ፡-** ሙስና ከሥነ ምግባር ውጪ የሆነ ተግባር ተቀባይነት የሚገኝበት የስራ ቦታ ባህል እንዲፈጠር ያደርጋል። ለምሳሌ እንደ ቮልስዋገን ባሉ ድርጅቶች ውስጥ የልቀት ማጭበርበርን የሚፈቅደው ባሕል ብዙዎች ከሥነ ምግባር

ውጭ የሆነ ድርጅት አካል እንደሆኑ ስለሚሰማቸው የሰራተኞች ሞራል እንዲቀንስ አድርጓል፡፡ ማለትም ሰራተኞቹ ከሥነ ምግባር ውጭ የሆኑ ድርጊቶችን እንዲፈጽሙ ግፊት እንደተሰማቸው እና ይህም ወደ ሰፊ እርካታ ማጣት ኢንደፈጠረ ገልጸዋል፡፡

- **የሰራተኞች ከስራ መልቀቅ፡-** ከፍተኛ ሙስና የሰራተኞች ከስራ መልቀቅ እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል፣ ምክንያቱም ብዙውን ግዜ ጎበዝ ሰራተኞች ጠንካራ የስነምግባር ደረጃ ባላቸው ድርጅቶች ውስጥ ስራ ይፈልጋሉ፡፡ የኤንሮን ቅሌት ብዙ ሰራተኞችን ከሥነ ምግባር ውጭ በሆነ አሠራሩ ከድርጅቱ እንዲለቁ ያደረገ ሲሆን ልምድ ያላቸው ሰራተኞቹ መልቀቃቸው ድርጅቱን የበለጠ እንዲዳከም አድርጎታል፡፡

## ሐ. ደካማ ውሳኔ አሰጣጥ እና አግባብ ያልሆነ የሀብት ድልድል

- **ደካማ ውሳኔ አሰጣጥ፡-** ውሳኔዎች ከድርጅቱ ጥቅም ይልቅ በጉቦ ወይም በግል ጥቅም ተጽዕኖ ስለሚወሰን ሙስና ብዙውን ጊዜ ወደ ደካማ ውሳኔዎች ይመራል፡፡ የ1ኤምዲቢ ቅሌት የመልካም አስተዳደር እጦት እና ሙስና አስከፊ የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች የተወሰነበት እና የማሌዢያ ግብር ከፋዮች ላይ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ኪሳራ ያስከተለ ግልፅ ምሳሌ ነው፡፡
- **አግባብ ያልሆነ የሀብት ድልድል፡-** ሙስና ገንዘቦች አስፈላጊ ከሆኑ ፕሮጀክቶች ወደ አላስፈላጊ ወደ ሆኑ ፕሮጀክቶች እንዲዘዋወሩ በማድረግ ሀብትን አላግባብ ወደ መመደብ ሊያመራ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በታዳጊ ሀገራት በሕዝብ አገልግሎቶች ውስጥ ለቴክኖሎጂ ማሻሻያ ተብሎ የታሰበ ገንዘቦች ብዙ ጊዜ ስለሚባክኑ በቂ ያልሆነ መሠረተ ልማት እና አገልግሎቶች እንዲኖሩ ደርጋል፡፡

## 4. የቴክኖሎጂ ጉዳቶች

### ሀ. ፈጠራ ያቀዛቅዛል

**በምርምር እና ልማት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት መቀነስ፡-** ሙስና ገንዘቦችን ከምርምር እና ልማት ወደ ሌላ በማዞር ለፈጠራ ያለውን ሃብት ይገድባል፡፡ ተቋማት ሙስናን ለመሸፈን ከፍተኛ ግብአት ሲመድቡ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመስራት ወይም ያሉትን ለማሻሻል የሚኖረው የገንዘብ ድጎማ ያንሳል፡፡ ለምሳሌ በብራዚል፣ በመንግስት ባለቤትነት ስር ያሉ እንደ ፔትሮብራስ

ባሉ ድርጅቶች በሙስና ምክኒያት የምርምር እና ልማት በጀት እንዲቀንስ በመደረጉ በነዳጅ እና ጋዝ ዘርፍ እና ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎች ላይ ፈጠራን ማቀዛቀዝ ተችሏል።

**ለ. የምርት ጥራት እና ደህንነት አለመኖር**

- **በምርት ልማት ሂደት አቋራጮች መጠቀም፡-** ሙስና ድርጅቶች ለምርት ልማት አቋራጭ መንገድ እንዲወስዱ እና ከጥራት እና ከደህንነት ይልቅ ለፍጥነት እና ዋጋ ቅድሚያ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። ይህም ደረጃ ያልጠቁ ምርቶች ወደ ገበያ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይችላል.
- **የሸማቾች ደህንነት ስጋቶች፡-** በምርት ልማት ላይ የሚደርሰው ሙስና በተጠቃሚዎች ደህንነት ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትል ይችላል። ድርጅቶች ሥነ ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን ሲፈጽሙ፣ አስፈላጊ የደህንነት ደረጃዎችን ችላ ሊሉ ይችላሉ። ለምሳሌ በቻይና፣ የወተት ቅሌት ኩባንያዎች ትርፍን ለመጨመር በወተት ምርቶች ላይ ጎጂ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን በመጨመር በተጠቃሚዎች ላይ ከፍተኛ የጤና አደጋን አስከትሏል። ይህ ክስተት የሙስናን አደጋ እና የቁጥጥር ማነስን አጉልቶ አሳይቷል።

**ሐ. የሳይበር ደህንነት ስጋቶች**

- **በቸልተኝነት ምክንያት የተጋላጭነቶች መጨመር፡-** ሙስና የሳይበር ደህንነት ተግባራትን ቸል እንዲባል ሊያደርግ ይችላል ምክኒያቱም ድርጅቶች ተገቢው የደህንነት እርምጃዎች ላይ ኢንቨስት ከማድረግ ይልቅ ለሙስና ተግባራት ቅድሚያ ሊሰጡ ስለሚችሉ ነው። ይህ ቸልተኝነት ድርጅቶችን ለሳይበር ጥቃቶች ተጋላጭነትን ይጨምራል። ለምሳሌ፡ እ.ኤ.አ. በ2017 የEquifax መረጃ መጣስ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሚስጥራዊነት ያላቸው የግል መረጃዎችን በቂ ባልሆኑ የደህንነት ተግባር ምክኒያት ተጋልጧል። በቀጥታ የሙስና ጉዳይ ባይሆንም፣ ሥርዓታዊ ቸልተኝነት እንዴት ወደ ከፍተኛ የሳይበር ደህንነት ስጋቶ እንደሚዳርግ ያሳያል።
- **ለዳታ መጣስ እና ማጭበርበር ስጋት መሆን፡-** ሙስና የመረጃ ጥሰት እና ማጭበርበር የበለጠ ሊፈጠር የሚችልበትን ሁኔታ ይፈጥራል። ድርጅቶች የሥነ ምግባር ደረጃዎችን ማክበር ሲያቅታቸው፣ የመረጃ ጥበቃ ፕሮቶኮሎችንም ችላ ሊሉ እና ይህም ወደ ከፍተኛ ስጋቶች ሊያመራ ይችላል። ለምሳሌ፡ በህንድ በአድሃሃር ስርዓት ውስጥ ያለው ሙስና በመረጃ ደህንነት ላይ ስጋት ፈጥሮ ነበር፣ በዚህም የተነሳ ሚስጥራዊ የሆኑ የግል

መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በአያያዝ ላይ አላግባብ መጠቀም እና ማጭበርበር ክስ ተመስርቶበታል፡፡

ሙስና በኢኖቬሽን እና በቴክኖሎጂ ዘርፍ ከፍተኛ ቴክኖሎጂያዊ ጉዳቶች ሲኖሩት ይህም ፈጠራን ይገታል፣ ጥራትን እና ደህንነትን ይጎዳል እንዲሁም የሳይበር ደህንነት ስጋቶችን ይጨምራል፡፡

## 3.3 በአስረጅ ናሙና (ኬዝ) ላይ የተመሰረተ ልምምድ

ይህ መልመጃ ተሳታፊዎች በተቋም ውስጥ ያሉ ተለያዩ የስራ ክፍሎች ውስጥ ያለን የሙስና ተጋላጭነት ሁኔታን፣ መገለጫዎችን እና ምክንያቶችን እንዲመረምሩ ለመርዳት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ልምምዱ ሰልጣኞች  በጥልቀት እንዲያስቡ፣ የሙስና ስጋት ምክንያቶችን እና የተለዩ የሙስና ስጋቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን እንዲያዘጋጁ ያስችላቸዋል፡፡

**የአስረጅ ናሙና መልመጃ**

**አስረጅ ናሙና 1፡ የሳተላይት ቴክኖሎጂ እና የሶፍትዌር ግዥ**

የX አገር መንግስት የሀገሪቱን የስፔስ ሳይንስ አቅም በማሳደግ የሳተላይት ቴክኖሎጂን በማዳበር የእርሻ መሬት አጠቃቀምን ለመቆጣጠር፣ የአካባቢ ለውጦችን ለመከታተል እና የአደጋ ምላሽን ለማሻሻል በማሰብ ተቋም አቋቁሞዋል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2023 ተቋሙ "LandWatch" የተሰኘ አዲስ ፕሮጀክት በማዘጋጀት ለሳተላይት ልማት፣ ለመሬት መሠረተ ልማት እና ለሰራተኞች ስልጠና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ እና የመንግስት ድጋፍ ማግኘት ችሎዋል፡፡ የፕሮጀክቱ አላማም የአገሪቱን መልከአ ምድራዊ ስእል ለማንሳት የሚያስችል የሳተላይት ሲስተም በመዘርጋት በመሬት አጠቃቀም ላይ ለውጦችን ለመከታተል እና ለፖሊሲ አውጪዎች ጠቃሚ መረጃዎችን ማቅረብ ነው፡፡

ፕሮጀክቱን መተግበር በሚጀምርበት ወቅት የተቋሙ ከፍተኛ  አመራሮች የፕሮጀክት ትግበራ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ እራሳቸውን የፕሮጀክት ክትትል ኮሚቴ አባላት በማድረግ የፕሮጀክቱ 10% ፈንድ ለኮሚቴው የማማከር ክፍያ ተብሎ እንዲከፍለው ወስነዋል፡፡ በትግበራ ወቅት ተቋሙ ለፕሮጀክቱ የሳተላይት ቴክኖሎጂ እና ሶፍትዌር መግዛት በመፈለጉ ጨረታ ወጥቶ በርካታ ኩባንያዎች በጨረታው ወቅት ፕሮፖዛል አቅርበው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ጨረታውን በዘርፉ ብዙም ልምድ የሌለው እና የተቋሙ ዳይሬክተር ወንድም የሆነው Y ኩባንያ ጨረታውን

አሸንፏል፡፡  ግዥው ከፍተኛ ቴክኒካል አገልግሎት ስለሆነ የግዢው ሂደት ግልፅ ስላልነበረ የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነው አቶ X ከኩባንያው ባለቤት ከፍተኛ ገንዘብ በመቀበል ጨረታውን እንዲሸንፍ እርጓል፡፡

አሸናፊው ድርጅት አዲስ እና በዘርፉ ልምድ ያለው ስላልሆነ ስራውን ለመስራት የሚስችለው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የሰው ኃይል  አልነበረውም፡፡ በዚህ ምክልኒያት የሳተላይት ምስሎችን በኋላቀር መሳሪዎች የተነሱ በመሆኑ አሁን ያለውን የአገሪቱን የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ ማሳየት ባለመቻላቸው ፕሮጀክቱ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

### የውይይት ጥያቄዎች

1. ከላይ በተነሳው ኬዝ ውስጥ ሙስና ተከስቷል? በማን ምን አይነት ሙስና ተፈፅሟል?
2. በእናንተ አመከላከት ግለሰቦቹ ሙስና ውስጥ እንዲሳተፉ ያስገደዳቸው ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
3. ሙስናው በፕሮጀክቱ አጠቃላይ ስኬት ላይ እንዲሁም በአገሪቱ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳድሯል ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. ወደፊት እንደዚህ አይነት የሙስና ተግባራትን ለመከላከል ምን አይነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው?
5. ሰራተኞች በድርጅታቸው ውስጥ ሙስናን በመከላከል ረገድ ምን ሃላፊነት አለባቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

### አስረጅ ናሙና 2፡ የስታርት አፕ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ማጭበርበር

ወይዘሮ ሃና  ለፈጠራ ቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶች የሚሰጠውን ድጎማ የማስተዳደር ለስራ ክፍላቸው ኃላፊነት የተሰጣቸው መካከለኛ አመራር ናቸው፡፡ የፈንድ አሰጣጥ ስርአቱን በደንብ እያወቀች ስትሄድ፣ ስርዓቱን ለግል ጥቅም የምትጠቀምባቸውን አጋጣሚዎች አስተዋለች፡፡ ይህንንም ለማሳካት  ወይዘሮ. ሃና ከተለያዩ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት ስለነበራት ከአመልካቾች ጉቦ መጠየቅ ጀመረች፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ትልቅ የገንዘብ እገዛ የሚፈልግ የግብርና ቴክኖሎጂ ኩባንያ የእርዳታ ማመልከቻቸውን በፍጥነት እንዲፀድቅለት የገንዘብ ስጦታ አቀረበላት፡፡ ይህንን ጉቦ በመቀበል፣ ወይዘሮ ሃና የፕሮጀክቱን ጥቅም በበቂ ሁኔታ እንዲገመገም ሳታደርግ ለድርጅቱ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጥ አደረገች፡፡ ይህም የፋይናንስ ሂደቱን ታማኝነት ከማሳጣት

ባለፈ የግብርናውን ዘርፍ ሊጠቅሙ ከሚችሉ እውነተኛ ፈጠራ ፕሮጀክቶች ላይ ግብአት እንዳይውል አድርጓል።

በድጋፍ አሰጣጡ ሂደት፣ ወይዘሮ ሃና አንዳንድ ተመራማሪዎች መረጃቸውን እንዲቀይሩ ግፊት አድርጋለች። ያገኙትን የገንዘብ ድጋፍ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የምርምር ቡድኖች የቴክኖሎጂያቸውን ውጤታማነት አጋንነው እንዲያሳዩ መመሪያ በመስጠቷ ቡድኑም ድጋፉን እንዳያጣ በመመሪዋ ተስማምቶዋል። ይህ የወ/ሮ ሀና ተግባር ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ ፕሮጀክቶችን እንዲፀድቅ አድርጓል እንዲሁም የግብር ከፋዩን ገንዘብ በማባከን እና እውነተኛ የቴክኖሎጂ እድገትን እንቅፋት ሆኗል። ከገልዘብ ድጋፍ ማመልከቻውች ውስጥ የሷም ማመልከቻ ቢኖርም ይህንን ጉዳይ ለተቋሙ አላሳወቀችም። ስለሆነ አመልካቹች ማመልከቻ በሚያስገቡበት ግዜ የራሷን ፕሮጀክት ቅድሚያ በመስጠት ያለ ውድድር እንዲልፍ አድርጋለች። ይህ አድሎአዊነት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ላይ ያለውን እምነት ከመሸርሸር ባለፈ ለፕሮጀክቱ ስኬት የማይታሰብ ሃብት እንዲመደብ አድርጓል።

ወ/ሮ ሃና የድጋፍ ማመልከቻዎችን እና የገንዘብ ድጎማዎችን በተመለከተ መረጃ ባታጋራም ለምትቀራረባቸው ኩባንያዎች በቀጣይ ስለሚሰጥ የመንግስት እርዳታ ሚስጥራዊ መረጃ ሰጥተዋል። ይህ የውስጥ አዋቂ መረጃ እነዚህ ኩባንያዎች ሃሳቦቻቸውን ቀድመው እንዲያዘጋጁ በማስቻል መረጃ ከሌላቸው ተፎካካሪዎች ይልቅ ፍትሃዊ ያልሆነ ጥቅም እንዲያገኙ አድርጋለች። ይህ ግልጽነት የጎደለው ተግባር ያለ ተጠያቂነት እንድትንቀሳቀስ አስችሎታል እና እውነተኛ ፈጣሪዎች ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር እንዳይተባበሩ አድርጓል። ወይዘሮ ሃና ህዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ ከታሰበው ገንዘብ የራሷ ድርጅት የድጋፉ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ገንዘብ ወስዳለች። ይህ አላግባብ መጠቀም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የተደራሽነት ጥረቶችን ውጤታማነት የሚገድብ ከመሆኑም በላይ ለሚገባቸው ፕሮጀክቶች ያለውን ግብአት ቀንሷል።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ከላይ በተነሳው ኬዝ ውስጥ ሙስና ተከስቷል? በማን ምን አይነት ሙስና ተፈፅሟል?
2. በእናንተ አመከላከት ግለሰቦቹ ሙስና ውስጥ እንዲሳተፉ ያስገደዳቸው ምክኒያት ምን ይመስላችኋል?

3. ሙስናው በፕሮጀክቱ አጠቃላይ ስኬት ላይ እናዲሁም በአገሪቱ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳድሯል ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. ወደፊት እንደዚህ አይነት የሙስና ተግባራትን ለመከላከል ምን አይነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው?
5. ሰራተኞች በድርጅታቸው ውስጥ ሙስናን በመከላከል ረገድ ምን ሃላፊነት አለባቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

## አስረጅ ናሙና 3፡ የፈጠራ ባለቤትነት ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሙስና

በየእምሮአዊ ንብረት ምዝገባ ተቀቋም ውስጥ፣ የባለቤትነት መብትና የንግድ ምልክቶች ምዝገባን የመቆጣጠር ኃላፊነት የነበረው አቶ ታዬ የሚባል ከፍተኛ ባለሥልጣን ነበር። በግላዊ የፋይናንስ ጫና እና በተቀቋሙ ዉስጥ ባለዉ የሙስና ባህል አማካኝነት በተቀቋሙ እና በኢትዮጵያ ባለው ሰፊ የአእምሯዊ ንብረት ገጽታ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ሥነ ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶች ውስጥ መሳተፍ ጀመረ። ተጽእኖ ስር በመሆን በድርጅቱ እና በኢትዮጵያ ያለው ሰፊ የአይ.ፒ.
የአቶ ታዬ የመጀመሪያ ሙስና ተግባር የተፋጠነ የንግድ ምልክት ምዝገባ ከሚፈልጉ ኩባንያዎች ጉቦ መቀበል ነበር። ለምሳሌ፣ አንድ ታዋቂ የመጠጥ ኩባንያ አዲሱን የንግድ ምልክታቸውን ለማፀደቅ መደበኛ ግምገማ ሂደት ለማለፍ ብዙ ገንዘብ በመስጠት ወደ እሱ ቀረበ። አቶ ታዬ ይህንን ጉቦ በመቀበል የንግድ ምልክቱ አስፈላጊውን ህጋዊ አሰራር ሳይከተል እንዲመዘገብ ሁኔታዎችን አመቻችቶ ኩባንያው ያለጊዜው እንዲጠቀምበት አስችሏል። ይህ ድርጊት የአእምሯዊ ንብረት ሥርዓቱን ታማኝነት በመሸርሸር የሸማቾች ውዥንብር እንዲፈጠር እና ዝቅተኛ ወይም ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ምልክቶች እንዲመዘገቡ በማድረግ ገበያውን አዛብቷል።
ስለ አእምሯዊ ንብረት መብቶች ለህዝብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎች የተመደበው ገንዘብ በአቶ ታዬ አስተዳደር ስር እንደመጣ፣ እነዚህን ሀብቶች ለግል ጥቅማጥቅም ሲል አላግባብ መድቧል። ገንዘቡን ስለ አእምሯዊ ንብረት መብቶች እና አስፈላጊነታቸው ህብረተሰቡን ከማስተማር ይልቅ ወደ ውጤታማ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች መርቷቸዋል ወይም ወደ ራሱ አካውንት እንዲዘዋወሩ አድርጓል። ይህ የመልካም አስተዳደር እጦት ህዝቡ በቂ ግንዛቤ እንዳይኖረው አድርጓል፣ ፈጠራን ማደናቀፍ እና የሀገር ውስጥ ፈጣሪዎች እና ፈጣሪዎች ለአእምሯዊ ንብረት ስርቆት ተጋላጭ እንዲሆኑ አድርጓል።
በተጨማሪም አቶ ታዬ የፓተንት ማመልከቻዎች፣ የተፈቀደላቸው እና የማስፈጸሚያ ተግባራት መረጃ ለህዝብ ተደራሽ አለመሆናቸውን በማረጋገጥ ባለድርሻ አካላት ባለስልጣኑን ተጠያቂ

ለማድረግ አዳጋች ሆነዋል። ይህ ግልጽነት የጎደለው ነገር በፈጣሪዎች እና በንግዶች መካከል አለመተማመንን ፈጥሯል፣ ከአእምሮአዊ ንብረት ስርዓት ጋር እንዳይተባበሩ እና የአእምሯዊ ንብረት ስርቆት እድል እንዲጨምር አድርጓል፣ ምክንያቱም ቁጥጥር በማይደረግበት ጊዜ ሊጥሱ የሚችሉ ሰዎች ድፍረት ስለሚሰማቸው።

በሌላ የሥነ ምግባር ጉድለት፣ አቶ ታዬ ለተወሰኑ አመልካቾች ደጋፊ ለመሆን መዝገቦችን አጭበርብረዋል። ማመልከቻዎቻቸው ህጋዊ መስፈርቶችን ባያሟሉም ከግል ግንኙነታቸው ጋር ለተገናኙ ኩባንያዎች የባለቤትነት መብት ለመስጠት የምዝገባ ሰነዶችን ለውጧል። ይህ አሰራር ትክክለኛ ያልሆኑ የፈጠራ ባለቤትነት ማረጋገጫዎችን በማውጣት ህጋዊውን ገጽታ ለእውነተኛ ፈጣሪዎች በማወሳሰብ እና ለፍትሃዊ ውድድር እንቅፋት ፈጥሯል።

### የውይይት ጥያቄዎች

1. በአቶ ታዬ የወሰዷቸው ተግባራት ሙስናን የሚያሳዩት የትኞቹ ናቸው?
2. አቶ ታዬ ወደ ብልሹ አሰራር እንዲገቡ ያደረጋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. የአቶ ታዬ ብልሹ አሰራር የድርጅቱን ታማኝነት እና ተልዕኮ እንዴት ነካው?
4. ድርጅቶቹ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን ምን አይነት እርምጃዎችን ሊተገብሩ ይችላሉ?

### አስረጅ ናሙና 4፡ የአቶ አለሙ የሙስና ተግባር እና ምክኒያቶች

አቶ አለሙ የቴክኖሎጂ ፈጠራ እና የምርምር ፕሮጀክቶችን የመቆጣጠር ሃላፊነት ባለው የመንግስት የቴክኖሎጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ውስጥ የመካከለኛ ደረጃ ስራ አስኪያጅ ነው። ባለሥልጣኑ ግልጽ ያልሆነ የሥልጣን ተዋረድ እና ተጠያቂነት ስላለው በሠራተኞች መካከል ግራ መጋባትን አስከትሎዋል። በግራንት (ፕሮጀክት ገንዘብ) ድልድል ሂደት ወቅት፣ አንድ የሥራ ባልደረባው ተገቢው ግምገማ ሳይደረግ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ከተመረጠ ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ ጋር እየሰራ መሆኑን ደርሶበታል። ይህን ተግባር ለማን ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት ግልፅ ስላልሆነለት ከድጋፍ ገንዘብ ትንሽ ገንዘብ በመቶኛ ለመቀበል እና ዝም ለማለት ተስማማ።

ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በኢኮኖሚ ውድቀት ሳቢያ የበጀት ቅነሳ ላይ ስለሆነ ሠራተኛው በውስን ሀብት ውጤት ማስገኘት እንዳለበት መመሪያ ተላልፎለት ጫና ውስጥ ገብቶዋል። ይሁን እንጂ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ የሚጠይቀውን ፕሮጀክት የመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት አቶ አለሙ የተጋነነ የበጀት ግምት በማቅረብ ትርፍ ገንዘቡን ወደ ኪሱ አስገብቶዋል። የተቋሙ የበጀት ቅነሳ ትርፍ ስራዎች እንዳይሰሩ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዳይከፈል ስለሚከለክል የፕሮጀክት

በጀቶችን ከፍ አድርጎ በማስያዝ ልዩነቱን ለግል መጠቀም ለመኖር አስፈላጊ ነው ብሎ አምኗል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የፕሮጀክት አፈጻፀምን ከፍ አድርጎ ለማሳየት ሪፖርቶችን እንዲያጭበረብር ግፊት ሲደረግበት የሥራውን ደህንነት ለማስጠበቅ ማድረግ እንዳለበት አምኖ ትእዛዙን ያሟላል፡፡ የመንግስት የፖለቲካ ሹመኞችም እያንዳንዱ የሚፈቅዱት የፕሮጀክት የአበል ክፍያዎች ላይ ባይሳተፉም ስማቸው ለክፍያ እንዲተላለፍ እንደሚጠብቁ ስለሚያውቅ እነሱን በክፍያዎች ላይ ማሳተፍ ለፕሮጀክቱ ፍጥነት አስፈላጊ ነው ብሎ ስለሚያምን ክፍያዎች በኖሩ ቁጥር ክፍያው ባይገባቸውንም እንዲከፈላቸው ያደርጋል፡፡

የአቶ አለሙ እና ሌሎች ሰራተኞች ተግባራት የተቋሙ የስራ አካባቢ መጥፎ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ በሰራተኞች መካከል የእርስ በርስ መተማመን እንዳይኖር አድር፡፡ በተቋ ውስጥ ሲከናወን የቆየው ሙስናው ውሎ አድሮ ሲጋለጥ ህዝቡ እና ለጋሽ ድርጅቶ በተቋሙ ላይ ያላቸው እምነት ተሸርሽሯል፡፡ ይህ የእምነት ማጣት ማጣት ለቴክኖሎጂ እና ለፈጠራ ምርምር እድገት አስፈላጊ የሆኑትን አስፈላጊ ትብብር ተቋ እንዲያጣ አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክኒያት ወሳኝ ፕሮጀክቶች ቆመዋል፣ በጤና አጠባበቅ እና በአካባቢያዊ ዘላቂነት ላይ የተሰሩ ለህብረተሰቡን በእጅጉ ሊጠቅሙ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች እንዲቆሙ ሆነዋል፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. አቶ አለሙን ሙስና ውስጥ እንዲገቡ ያደረጋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? የአቶ አለሙ እና የስራ ባልደረቦቻቸው በተቋሙ ውስጥ በሰሩት የሙስና ተግባር ምን ጉዳት መጥቷል? ማን ተጎድቷል?
2. ተቋሙ ሙስናን ለመከላከል እና በሰራተኞቹ መካከል ስነምግባርን ለማስፈን ምን እርምጃዎች መውሰድ አለበት?
3. የቴክኖሎጂ ውጠቶች በተቋት ውስጥ የሙስና አደጋዎችን በመቅረፍ ረገድ ምን ሚና አላቸው?
4. ሠራተኞች ደህንነነታቸው ተጠብቆ ሥነ ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን ሪፖርት ለማድረግ ድርጅቱ ምን ዓይነት እርምጃዎችን መተግበር አለበት?

## 3.4 የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከያ ስልቶች

### 3.4.1. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው። ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቅው ሊያውቁ ይገባል። ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል። በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው። ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል።

### 3.4.2. ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

#### ሀ. ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው። ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም።

ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል።
በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም። ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም።

#### ለ. ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው። ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል። ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ

አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡

### 3.4.3. የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

### 3.4.4. የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጩ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

### 3.4.5. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን

የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

### 3.4.6. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

### 3.4.7. የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቻ ሙሽናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፦

- በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣

- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭትን የመከላከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

### 3.4.8. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል፡፡ እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል፡፡

### 3.4.9. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

### 3.4.10. የሙስና ስጋት ግምገማ እና አስተዳደር

በአሰራር ሂደት ላይ ያሉ የሙስና አደጋዎችን መለየት፡- የሙስና ስጋት ግምገማ በተለያዩ ተቋማዊ አሰራር ሂደቶች ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን መለየት እና መተንተንን ያካትታል፡፡

ይህ አካሄድ ተቋማቶች ወደ ብልሹ አሰራር ከመምራታቸው በፊት ቀድመው እነዚህን አደጋዎች ለመቀነስ ወይም ለመከላከል የመከላከያ ስልቶን እንዲተገብሩ ያስችላቸዋል፡፡ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የተባለው ተቋማትን የሙስና ስጋት ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችሏቸውን መመሪያዎችን ይሰጣል፡፡ እነዚህ ግምገማዎች ተቋማት እንደ ግዥ እና ፋይናንሺያል አስተዳደር ባሉ አካባቢዎች ያሉ ተጋላጭነቶችን እንዲለዩ እና ተስማሚ የመቆጣጠሪያ ስልቶችን በቅረፅ እና በመተግበር የሙስና እድሎችን መቀነስ ያስችላቸዋል፡፡

የሙስና ስጋት ሁል ግዜ የሚኖር ስለሆነ ተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ግምገማ በየግዜው ማድረግ የሚገባቸው ቢሆንም ሁሉም የፌደራል የመንግስት ተቋማት ይህን ተግባር አያከናውኑም ማለት ይቻላል፡፡ በ2016 ዓ.ም. የኤትዮጵያ ፌደራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን በ12 ዘርፎች የ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት አካሂዶ የዘርፎቹን የስጋት አካባቢዎች ለመለየት አስችሏል፡፡ ይህም የዘርፎቹን ልዩ ተጋላጭነት ከግምት ያስገቡ የመከላከያ ስልቶችን ለመተግበር ያስችላል፡፡

**መደበኛ ክትትል እና ሪፖርት፡-** መደበኛ ክትትል እና ሪፖርት የማድረግ ሂደት የጸረ-ሙስና ፖሊሲዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ እና ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመለየት ድርጅታዊ ሂደቶችን እና አሰራሮችን ስልታዊ በሆነ መልኩ መገምገምን ያካትታል፡፡ ይህ ቀጣይነት ያለው ቁጥጥር ተጠያቂነትን ለማስጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡- መደበኛ ክትትል ተቋማዊ ግልጽነትን ያሳድጋል እና በተገኘ ሙስና ላይ ፈጣን እርምጃ እንዲወሰድ ስለሚያስችል የታማኝነት ባህልን ያጠናክራል፡፡

### 3.4.11. የቅሬታ መስተንግዶ ሥርዓት መዘርጋት

ተቋሞች ባለጉዳዮች ከአንድ ተቋም ሊያገኟቸ የሚገቡ አገልግሎቶች እና አገልግሎት ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በማሳወቅ፣ የተጠያቂነትን ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ተገልጋዩ ተቋሙ ባስቀመጠው ደረጃ መሰረት አገልግሎት የማያገኝ ከሆነ ከሆነ ቅሬታ የሚያቀርብበት እና ፈጣን መልስ ሊያገኝ የሚችልበት የቅሬታ ማስተናገጃ ስርአት መዘርጋት ሙስናን ለመከላከል ወሳን ስልት ነው፡፡

**ተግባር 3.1 ማነቃቂያ ጥያቄ**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡
እንደ አንድ ዜጋ እና ሰራተኛ በዘርፉ ውስጥ ሙስናን በመከላከል ሂደት አስተዋጽኦ አለኝ ብለው ያምናሉ? ምን ማድረግ ይችላሉ?

## 3.5. ሙስናን በመከላከል የሰራተኞች ሚና

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሰራተኞች በፀረ-ሙስና ትግል ውስጥ ወሳኝ ቦታ ይይዛሉ:: የሰራተኞች ተግባር፣ ውሳኔዎች እና ለስነምግባር ደረጃዎች ያላቸው ቁርጠኝነት የተቋማትን ታማኝነት እና መልካም ስም በእጅጉ ሊጎዳ ይችላል:: ይህ ክፍል ሰራተኞች ሙስናን ለመዋጋት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉባቸውን መንገዶች ይዘረዝራል::

1. **የስነምግባር ደረጃዎችን መረዳት**
   - ***ፖሊሲዎችን ማወቅ፡-*** ሰራተኞች ስለ ተቋማቸዉ የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች እና የስነምግባር ደረጃዎች እውቀት ያላቸው መሆን አለባቸው:: ለምሳሌ፣ የቴክኖሎጂ ኩባንያ ስጦታዎችን እና መዝናኛዎችን በተመለከተ ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት የሚገልጽ ግልጽ የሆነ የስነምግባር ደንብ ሊኖረው ይችላል:: ከእነዚህ መመሪያዎች ጋር መተዋወቅ ሰራተኞቹ ብልሹ ባህሪን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል::
   - ***ለታማኝነት ቁርጠኛ መሆን፡-*** ተግባራትን ሥነ ምግባራዊ ሆኖ በመፈጸም፣ ሠራተኞች ለባልደረቦቻቸው ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ:: ይህ ቁርጠኝነት ተቋማቸዉ ውስጥ የታማኝነት ባህልን ያዳብራል:: ለምሳሌ፡ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ በቡድን ስብሰባዎች ወቅት የፕሮጀክት ዘገባን በተመለከተ የታማኝነትን አስፈላጊነት በመደበኝነት ያወያያል፣የቡድን አባላት ስለ ተግዳሮቶች እና መሰናክሎች ግልጽ እንዲሆኑ ያበረታታል::
2. ***ሪፖርት ማድረግ እና መጠቆም***
   - ***ሪፖርት እንዲያደርጉ ማበረታታት፡*** ሰራተኞች አጠራጣሪ ድርጊቶችን ወይም ስነምግባር የጎደላቸው ድርጊቶችን ሪፖርት የማድረግ ስልጣን ያላቸዉ መሆኑን ሊሰማቸው ይገባል:: ተቋማት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሚስጥራዊ መንገዶችን ማዘጋጀት አለባቸው:: **ለምሳሌ** የሳይበር ደህንነት ተንታኝ በድርጅቱ የፋይናንሺያል ሶፍትዌር ውስጥ መደበኛ ያልሆኑ ግብይቶችን ቢያስተውል ስም እንዳይገለጽ ዋስትና በሚሰጠው የመረጃ ጠቋሚ የስልክ መስመር (whistleblower hotline) ተንታኙ ጉዳዩን ያለምንም ፍርሃት ሊያቀርብ ይችላል::
   - ***የጠቋሚዎችን ጥበቃ መረዳት*** (Understanding Whistleblower Protections) ፡- ስለ ጥበቃዎች ግንዛቤ መኖር ሰራተኞች የብቀላ ስጋትን ሳይፈሩ ጥቆማቸውን እንዲናገሩ ሊያበረታታ ይችላል:: ለምሳሌ ስለ ሙስና ጠቋሚ መብቶች ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ፣ ሰራተኞ በተቋማቱ የስነ ምግባር የጎደላቸው ድርጊቶችን የሚጠቁሙ ሰዎችን ለመጠበቅ

ፖሊሲዎች እንዳሉት ያውቃል። ይህም የስነምግባር ጉድለትን ሪፖርት ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎት ይጨምራል።

3. **በስልጠና ውስጥ ንቁ ተሳትፎ**
   - **በስልጠና ፕሮግራሞች መሳተፍ፡-** በፀረ-ሙስና ስልጠና ላይ መሳተፍ ሰራተኞቹ ስለሙስና መከላከል ወቅታዊ አዝማሚያዎች፣ አደጋዎች እና ምርጥ ተሞክሮዎች እንዲያውቁ ያግዛል።
   - **እውቀትን ማካፈል፡** ሰራተኞች በስልጠና ክፍለ ጊዜ ግንዛቤዎችን እና ልምዶችን ማጋራት፣ የትብብር የመማሪያ አካባቢን መፍጠር ይችላሉ። ለምሳሌ፡- አንድ ሰራተኛ በፕሮጀክት ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የጥቅም ግጭት ለይተው ያለፈ ልምድ ያካፍላሉ፣ይህም ወደፊት ተመሳሳይ ሁኔታዎችን እንዴት ማስተናገድ እንደሚቻል ተሳታፊዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል።

4. **ግልጽነትን ማሳደግ**
   - **ግልጽ ግንኙነትን ማበረታታት፡-** ሰራተኞች ስለ ስነምግባር ጉዳዮች እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ግልጽ ውይይት በማድረግ የግልጽነት ባህልን ማሳደግ ይችላሉ።
   - **ሂደቶችን መመዝገብ፡** ሰራተኞቻቸው የስራ ሂደቶቻቸውን እና ውሳኔዎቻቸውን በጥንቃቄ በመመዝገብ ተጠያቂነትን እና ክትትልን ለማረጋገጥ ይረዳሉ። ለምሳሌ የምርት ስራ አስኪያጅ የውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ግልፅ እና ተከላካይ መሆኑን ለማረጋገጥ የአቅራቢ ምርጫ መስፈርቶችን እና ግንኙነቶችን ዝርዝር መዝገቦችን መያዝ ይጠበቅበታል።

5. **የሙስና ስጋቶችን መለየት እና መቀነስ**
   - **በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ መሆን፡** ሰራተኞች በእለት ተእለት ተግባራቸው ንቁ ሆነው ሊቀጥሉ፣ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን በመለየት ለአመራሩ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ለምሳሌ፡ የፋይናንስ ሰራተኛ በወጪ ሪፖርቶች ላይ አለመግባባቶችን ቢያስተውል ለኃላፊ በማሳወቅ የውስጥ ቁጥጥርን እንዲጠናከር ሊያደርግ ይችላል።
   - **ለሙስና ስጋት ግብገማዎች አስተዋጽዖ ማድረግ፡-** በሙስና ስጋት ግምገማ ሂደቶች ውስጥ መሳተፍ ሰራተኞቹ ሙስና ሊፈጠር በሚችልባቸው አካባቢዎች ጠቃሚ ግንዛቤዎችን እንዲሰጡ ያስችላቸዋል። ለምሳሌ በሙስና ስጋት ምዘና አውደ ጥናት ወቅት፣ የአይቲ ሰራተኞች ለሶፍትዌር ፈቃድ ግዥ ሂደት ውስጥ ያሉ ድክመቶችን ያሳያሉ፣ ይህም ወደ ተሻለ ቁጥጥር ይመራል።

6. አወንታዊ የስራ አካባቢን ማሳደግ

- **በእኩዮች መካከል የስነምግባር ባህሪን ማበረታታት፡-** ሰራተኞች የስነምግባር ባህሪን በማስተዋወቅ እና ብልሹ አሰራሮችን በማስቆም የስራ ባልደረቦቻቸው ላይ ተጽእኖ ማሳደር ይችላሉ:: ለምሳሌ፡ አንድ ሰራተኛ የሚያጋጥሙትን ማንኛውንም ስነምግባር የጎደላቸው የአቅራቢዎችን አሰራር ሪፖርት የማድረግን አስፈላጊነት ለባልደረባው ያሳውቃል፣ የተጠያቂነት ባህልን ያሳድጋል::
- **የቡድን ታማኝነትን መገንባት፡** ከቡድን አጋሮች ጋር በመተባበር የስነምግባር ደረጃዎችን ማክበር በሙስና ላይ የጋራ ሀላፊነት ስሜት ይፈጥራል:: ምሳሌ፡ የቡድን መሪ በፕሮጀክታቸው ውስጥ ታማኝነትን ስለመጠበቅ ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉ በማበረታታት በስነምግባር ችግሮች ላይ መደበኛ ውይይቶችን ይጀምራል::

7. ከቴክኖሎጂ መፍትሄዎች ጋር መሳተፍ

- **የጸረ-ሙስና መሳሪያዎችን መጠቀም፡-** ሰራተኞች ሙስናን ለመለየት እና ለመከላከል የተነደፉ የቴክኖሎጂ መፍትሄዎችን ለምሳሌ compliance software እና የክትትል ስርዓት መጠቀም አለባቸው::
- **በቴክኖሎጂ ላይ ግብረመልስ መስጠት፡-** ሰራተኞች ሙስናን በመከላከል ረገድ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ውጤታማነት ላይ አስተያየት መስጠት፣ ተቋሞቻቸው ስርዓታቸውን እንዲያሻሽሉ መርዳት ይችላሉ::

**ተግባር 3.2 አስረጅ ናሙና፡ በእምሯዊ ንብረት ድርጅት የመረጃ ማቀበያ ገመድ (Whistleblowing Channel)**

በአንድ ሀገር (XXX) አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ምዝገባ ክፍል መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው አቶ አለማየሁ የድርጅቱን ፖሊሲዎች ለመረዳት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ለሰራተኞች በሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ በንቃት ይሳተፋል:: በእምሯዊ ንብረት ምዝገባ ሂደት ውስጥ ቅልጥፍናን እና ግልጽነትን ለማሳደግ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ፍላጎት ነበረው:: በስራው ወቅት አቶ አለማየሁ የእምሯዊ ንብረት ማመልከቻዎችን ማጭበርበርን የሚያካትቱ ተከታታይ ሥነ-ምግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን ተመልክቷል:: በርካታ ባልደረቦች ፈጣን ፍቃድ ከጠየቁ አመልካቾች ጉቦ እየተቀበሉ መሆኑን ተረድቷል፣ ይህም ያልተገባ የፈጠራ ባለቤትነት ፈቃድ እንዲፀድቅ እና በ XXX ሀገር የአእምሯዊ ንብረት ስርዓትን ታማኝነት እንዲጎዳ አድርጓል:: እነዚህ ብልሹ አሰራሮች በፈጠራ

እና በህዝብ አመኔታ ላይ የሚያደርሱትን አንድምታ ያሳሰበው አቶ አለማየሁ አዲስ የተቋቋመውን የመረጃ መጠቆሚያ ቻናል ለመጠቀም እና ለማጋለጥ ወሰነ። ይህ የመረጃ መጠቆሚያ ቻናል ሰራተኞች የስነምግባር የጎደላቸው ድርጊቶችን በሚስጥር እና ከሌሎች ሊደርስ የሚችለዉን በቀል ሳይፈሩ ሪፖርት እንዲያደርጉ ታስቦ የተሰራ ነዉ። አቶ አለማየሁ በመረጃ መጠቆሚያ ቻናል በኩል ዝርዝር ዘገባ ካቀረቡ በኂላ የጉቦ ስልቱን እና የሰነድ ማጭበርበርን በማስረጃ አስደግፈው ማንነታቸው በሚስጥር መያዙን አረጋግጠዋል። የ XXX ሀገር አእምሯዊ ንብረት ድርጅት ሁሉም የይገባኛል ጥያቄዎች በቁም ነገር መያዛቸውን እና በጥልቀት መመርመራቸውን በማረጋገጥ እንዲህ አይነት ሪፖርቶችን ለመመርመር ጠንካራ ፖሊሲ አለው። የምርመራ ቡድኑም ጠንካራ የውስጥ ምርመራ አድርጎ፣ ከምርመራ በኀላ ክሱን አረጋግጦ በርካታ ተሳታፊ ሰራተኞችን ከስራ አግዷል። የአቶ አለማየሁ ድፍረት የተሞላበት ተግባር አእምሯዊ ንብረት ድርጅት የውስጥ ቁጥጥርን እንዲያጠናክር ከማስቻሉም በላይ ህዝቡ በድርጅቱ ላይ ያለውን እምነት ወደነበረበት እንዲመለስ፣ የተጠያቂነት ባህል እንዲጎለብት እና ሌሎች ሰራተኞችም የስነምግባር የጎደላቸው ድርጊቶችን እንዲያሳዩ አበረታቷል።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. የአቶ አለማየሁ የመማር እና የስልጠና ንቁ አካሄድ ሙስናን ለይቶ እንዲያውቅ እና እንዲረዳው ያደረገው እንዴት ነው?
2. የXXX ሀገር የአእምሯዊ ንብረት ጠንካራ ሪፖርቶችን የመመርመር ፖሊሲ በየትኞቹ መንገዶች ነው የመረጃ ማስራጫ ጣቢያን ተአማኒነት የሚያጎላው?
3. አቶ አለማየሁ የመረጃ ማስራጫውን እንዲጠቀም ያነሳሳው ምንድን ነው?
4. ይህ የጉዳይ ጥናት ውጤታማ የመረጃ ማስራጫ ጣቢያዎችን ስለማቋቋም እና የታማኝነት ባህልን ስለማሳደግ ስላለው ጠቀሜታ ለሌሎች ድርጅቶች እንዴት ማሳወቅ ይችላል?

**ተግባር 3.3፡ መልመጃ**

ይህ የኬዝ ጥናት ልምምድ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የተሳካ የሙስና መከላከል ስልቶችን በማሳወቅ የተሳታፊዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ ያለመ ነው። የገሃዱ ዓለም ምሳሌዎችን በመተንተን፣ ስለተግባራዊነታቸው በመወያየት እና ውጤቶቻቸውን በማቅረብ ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ዘርፍ የፀረ-ሙስና ጥረቶች ላይ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ይረዳቸዋል።

**ዓላማ፡** ተሳታፊዎቹ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂው ዘርፍ ባሉ ተቋማት ውስጥ ሙስና ስጋቶችን በመለየት የመከላከል ስትራቴጂዎችን ይነድፋሉ እና ተግዳሮቶችን ይለያሉ፡፡

***መመሪያዎች፡-***

ተሳታፊዎችን ከታች ለተነሱት ጥያቄዎች ላይ ተወያይተው ሀሳባቸውን ለተሳታፊዎች ያቅርቡ

1. በተቋማችሁ ምን አይነት የሙስና ስጋት አለ
2. የሚስተዋሉ የሙስና መገለጫዎች የትኞቹ ናቸው
3. እነዚህ ክስተቶች ሲገኙ ወይም ሲጠረጠሩ የስራ ባልደረቦችዎ ወይም አለቆቹ ምን ምላሽ ሰጡ?
4. የተጠቀሱትን የሙስና ስጋቶች ለመከላከል በተቋማችሁ ውስጥ ምን አይነት ስልቶች ተተግብረዋል
5. እነዚህ የተተገበሩት ስልቶች ሙስናን በመቀነስ ረገድ ምን ያህል ውጤታማ ናቸው እንዴት
6. ተቋማችሁ ውስጥ እየተተገበረ ካለው የሙስና መከላከያ ስልት በተጨማሪ ምን አይነት የመከላከያ ስልቶች ቢተገበሩ ሙስናን የበለጠ መከላከል ይቻላል ብላችሁ ታስባላችሁ
7. በተቋማችሁ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡
8. የሙስና መከላከል ስልቶችን በተቋማችሁ ተግባራዊ ለማድረግ ሂደት የሚገጥሙ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው መፍትሄዎቻቸውስ፡፡

## 3.6. ማጠቃለያ

መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ

ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል። ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ስምንት ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል። ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል።

## 3.7. የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ይህን የስልጠና ክፍለ ጊዜ እንደጨረሱ፣ ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በመመለስ የክፍሉን የትምህርት አላማዎች ምን ያህል እንዳሳኩ እራስዎን የገልግሙ።

1. የሙስናን መከላከያ ስልተቶች ይዘርዝሩ።
2. የትኞቹ የሙስና መከላከል ስልቶች ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ውጤታማ ናቸው ብለው ያስባሉ
3. ከተጠቀሱት ስልቶች ውስጥ የትኞቹ በተቋማችሁ ውስጥ ተተግብረዋል?
4. ተቋማችሁ ሙስናን የመከላከያ ስልቶች በሚተገብርበት ግዜ ምን አይነት ተግዳሮቶች ገጥመውታል?

## የማስልጠኛ ሞጁሉ የማጠቃለያ ጥያቄዎች

በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተሳታፊ ሰልጣኞች መካከል ግንዛቤን ለማዳበር ተጨማሪ ጥያቄዎች፡-

1. **ሙስናን መረዳት፡-** በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሊፈጠሩ የሚችሉ ልዩ ልዩ የሙስና ዓይነቶች ምን ምን ናቸው? በዘርፉ ውስጥ ባሉ ተቋማት ያላቸው የሕዝብ አመኔታና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ያሳድራሉ?
2. **ስጋቶችን መለየት፡-** በኢትዮጵያ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የሙስና ስጋቶች ምንድን ናቸው ምክንያታቸውስ? እንደ አስተዳደር፣ ግልጽነት ማጣት እና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ያሉ ጉዳዮችስ ለእነዚህ ጉዳዮች እንዴት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ?
3. **የሙስና ጉዳቶችን መገምገም፡-** በኢትዮጵያ በፈጠራና በቴክኖሎጂ ዘርፍ በተለይም በኢኮኖሚ ልማትና በቴክኖሎጂ እድገት ላይ ሙስና ሊያስከትሉ የሚችሉ አደጋዎች እና የረጅም ጊዜ መዘዞች ምን ምን ናቸው?
4. **የፀረ-ሙስና ስትራቴጂዎችን ማሰስ፡** በፈጠራና በቴክኖሎጂ ዘርፍ ምን ልዩ የፀረ-ሙስና ስልቶች ሊተገበሩ ይችላሉ እና እነዚህ ስልቶች ዘርፉ የሚያጋጥመውን ልዩ የሙስና ስጋቶችን ለመከላከል እንዴት ሊያስችል ይችላሉ?

# ማጣቀሻዎች


1. Furlong, P. (2016). *Inside the Volkswagen Scandal: How the Company's Culture Fostered the Cheating*. Harvard Business Review. Retrieved from HBR.
2. **Government of Chile**. (2020). *Open Data Portal of Chile*. Retrieved from data.gov.cl
3. Healy, P. M., & Palepu, K. G. (2003). *The Fall of Enron*. Journal of Economic Perspectives, 17(2), 3-26.
4. Hechler Baer, M. (2008). Corporate Policing and Corporate Governance: What Can We Learn from Hewlett-Packard's Pretexting Scandal. *U. Cin. L. Rev.*, *77*, 523
5. Kattel, R., & Mazzucato, M. (2018). *Innovative Public Ownership: The Case of Estonia's E-Government*. *Journal of Economic Policy Reform*, 21(1), 1-20. DOI: 10.1080/17487870.2017.1367179
6. Kattel, R., & Mazzucato, M. (2018). *Innovative Public Ownership: The Case of Estonia's E-Government*. *Journal of Economic Policy Reform*, 21(1), 1-20. DOI: 10.1080/17487870.2017.1367179
7. Kaur, S. (2011). *The 2G Spectrum Scam: An Overview*. Economic and Political Weekly, 46(12), 15-17.
8. **Open Knowledge Foundation**. (2019). *Open Data in Latin America: A Comparative Study*. Retrieved from okfn.org
9. Tadesse, S. (2019). *Corruption in Ethiopia's Telecom Sector: A Case Study of Ethio Telecom*. Addis Standard. Retrieved from Addis Standard.
10. Transparency International. (2017). *Global Corruption Barometer*. Retrieved from Transparency International
11. Transparency International. (2020). *Corruption Perceptions Index 2020*. Retrieved from Transparency International
12. U.S. Department of Commerce. (2017). *ZTE Corporation and ZTE Kangxun Telecommunications Ltd. Settlement Agreement*. Retrieved from U.S. Department of Commerce.

13. U.S. Department of Justice. (2016). *Volkswagen AG Pleads Guilty to Criminal Charges in Connection with Emissions Fraud*. Retrieved from DOJ Press Release.
14. World Bank. (2019). *Business and Corruption: A Resource Guide for Small and Medium Enterprises*. Retrieved from World Bank
15. Zainul, A. (2018). *The 1MDB Scandal: Malaysia's Biggest Corruption Case*. Al Jazeera. Retrieved from Al Jazeera.
16. Zengler, T. (2017). *Wells Fargo: The Scandal That Shook the Banking World*. Harvard Business Review. Retrieved from HBR.

## ራስን መገምገሚያ ቼክሊስት

ይህን የስልጠና ሞጁል እንደጨረሱ ከዚህ በታች ለተቀመጡት አረፍተ ነገሮች አዎ ወይም አይ በማለት በመመለስ የስልጠናውን አላማዎች ምን ያህል እንዳሳኩ እራስዎን ይገምግሙ፡፡

| ተ.ቁ | መግለጫ | አዎ | አይ |
|---|---|---|---|
| 1 | የሙስናን ምንነት መግለፅ እና ከሌሎች ወንጀሎች የሚለይበትን ምክኒያቶች ለይቻለሁ፡፡ | | |
| 2 | የሙስናን የተለያዩ መገለጫዎችን(ለምሳሌ ጉቦ፣ ምዝበራ፣ ዘመድ አዝማድ) መለየት ችያለሁ፡፡ | | |
| 3 | ለሙስና መከሰት ምክኒያቶችን እና ሙስና በግለሰብ፣ በተቋም እና በአገር ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅእኖ ምን እንደሆኑ ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 4 | ሙስና በተለይ በኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ/ጉዳቶች እንደሚያሳድር ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 5 | ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍን ለሙስና እንዲጋለጥ የሚያደርጉ ስጋቶችን ለይቻሁ፡ | | |
| 6 | በስራ አካባቢዬ ውስጥ ያሉ ብልሹ አሰራሮችን ሊያመለክቱ የሚችሉ ቀይ ባንዲራዎች እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ | | |
| 7 | በፕሮጀክት አስተዳደርና አተገባበር ላይ የተለመዱ የሙስና ምልክቶችን መለየት ችያለሁ፡፡ | | |
| 8 | ሙስናን ለመከላከል የሚያግዙ የተለያዩ ስልቶች እንዳሉ ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | |
| 9 | ሙስናን በመከላከል እንደ አንድ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ የመንግስት ሰራተኛ ሚናዬን ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 19 | በምሰራበት ተቋም ውስጥ ስራ ለይ ያሉትን የስነ ምግባር ደንብ እና የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎች መረዳት እና መተገበር ሙስናን ለመከላከል ወሳኝ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 11 | የሙስናን ተግባር ወይም ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት ሪፖርት የማድረግ ሂደቶችን እና ሪፖርት ለሚያደርግ ሰው የሚደረጉ ጥበቃዎችን አውቃለሁ፡፡ | | |

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION
ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et